



# አማርኛ

## እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

### የመምህር መምሪያ



**አራተኛ ክፍል**

**በአዲስ አበባ ት/ቢሮ ተዘጋጅቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ እና በዲላ ትምህርት ኮሌጅ የተስማማ**

# አማርኛ ቋንቋ
# (እንደ አፍ መፍቻ)

## የመምህር መምሪያ

## ፬ኛ ክፍል

አዘጋጆች፡-

ዳንኤል ኃይለ ኢየሱስ(MA)
ህይወት ታምሩ (MA)
ሰለሞን ሰርካ (MA)

አርታዒ፡-
እንግዳወርቅ እንድርያስ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን የኢ.ፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እና በዲላ ትምህርት ኮሌጅ የቴክኒክ ድጋፍ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል፡፡

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢ.ፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው፡፡

# ማውጫ


ምዕራፍ አንድ (፩) ........ 1
የአከባቢ ጥበቃ ........ 1
ምዕራፍ ሁለት (፪) ........ 10
የመንገድ ደህንነት ........ 10
ምዕራፍ ሦስት (፫) ........ 25
መረዳዳት ........ 25
ምዕራፍ አራት (፬) ........ 9
ሥርዓተ-ጾታ ........ 10
ምዕራፍ አምስት (፭) ........ 25
ጉብኝት ........ 25
ምዕራፍ ስድስት (፮) ........ 39
ስፖርት ........ 39
ምዕራፍ ሰባት (፯) ........ 53
ውሃ ........ 53
ምዕራፍ ስምንት (፰) ........ 68
መደራደር ........ 68
ምዕራፍ ዘጠኝ (፱) ........ 80
መናገኛ ብዙኃን ........ 80
ምዕራፍ አስር (፲) ........ 94
ንግድ ........ 94

## መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የ4ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ለመጀመሪያ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው። በዚህ መጽሐፍ የሚማሩ ተማሪዎች በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት አካል ነው።

መጽሐፉ ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ተማሪዎች ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ በእኩል ደረጃ እንዴት እንደሚማሩ ማለማመድ ላይ የተመሰረተ ነው።

ይህ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት እና መርሃ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎች አካቷል።

1. ተማሪዎች ሥዕሎችንና ርዕሶችን በመመልከት የቅድመ ማዳመጥና ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲገምቱ በማድረግ ተረቶችን ወይም ታሪኮችን በማዳመጥና በማንበብ የማዳመጥና የማንበብ፣ የመጻፍና የመናገር ክሂላቸውን ያዳብራሉ።

2.ተማሪዎች የሚነበብላቸውን ታሪክ ወይንም ንባብ በሚገባ በማዳመጥና በማንበብ የአዳምጦ/የአንብቦ መረዳት በንግግርም ሆነ በፅሁፍ በግልፅ ቋንቋ መናገርና መፃፍ ይጠበቅባቸዋል። ይህንንም ለማድረግ ይችሉ ዘንድ በተከታታይ የመናገርና የመፃፍ ተደጋጋሚ ልምምድ እንዲያደርጉ ያግዟቸው።

3.ተማሪዎች ባዳመጡትና ባነበቡት ፅሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን እንደየአጠያየቃቸው የሚወክሏቸውን ፍቺ በመፃፍ በተገቢው የቃላት አሰዳደር ስርዓት በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያለማምዷቸው።

4. ተማሪዎች በተለመዱና በአዳዲስ ቃላት የተመሰረቱ ዓረፍተነገሮችን ማንበብ እንዲችሉ ልልምድ እንዲያደርጉ ያግዟቸው።

5.ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቻቸውን አብረው መማር አለባቸው፡፡ በዚህም የሚያደምጡትንና የሚያነቡትን ሃሳብ ይረዳሉ፡፡ የቃላት እውቀታቸውንም በማሳደግ በንግግርና በፅሁፍ ሃሳባቸውን በአግባቡ ይገልፃሉ፡፡

6. ተማሪዎች የተለያዩ የሰዋስው ተግባራትን በውስጠ ታዋቂነት እንዲሰሩ ሲደረግ አገልግሎቱ ላይ በመጠቀም እንዲረዱት ክትትልና ድጋፍ ያድርጓቸው ፡፡

## ለመምህር

ውድ መምህር ተማሪዎች የቋንቋን ትምህርት በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ የመምህራን እገዛ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግንዛቤ በማስገባት ተማሪዎችን በሚገባ ሊያግዟቸው ይገባል ፡፡

1. ለተማሪዎች የተለያዩ ታሪኮችን፣ ተረቶችን… ይንገሯቸው/ ያንብቡላቸው፡፡/
2. ለተማሪዎች የነገሯቸውን/ ያነበቡላቸውን ታሪክ/ ተረት ተማሪዎች መልሰው እንዲተርኩ/ እንዲናገሩ እንዲሁም የራሳቸውን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
3. በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችንና ተግባራትን እንደየመመሪያቸው በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው፡፡
4. ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የተለያዩ ፅሁፎችን እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
5. ለተማሪዎች በቤታቸው ተዘጋጅተው በመምጣት በተግባር እንዲያሳዩ የተለያዩ ተግባራትን ይስጧቸው፡፡

# ምዕራፍ አንድ (፩)

## የአከባቢ ጥበቃ

**የተሰጠ ክፍለ ጊዜ 9**

**ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የሚነበብላቸውን ምንባብ አዳምጠው መልዕክቱን ይናገራሉ፡፡
- በክፍል ደረጃቸው ያነበቡትን ጽሁፍ ዋና ሃሳብ ያለያሉ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ እና ፍካሬያዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- አያያዥ ቃል በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተነገር ይጽፋሉ፡፡

**የትምህርቱ ይዘቶች፡-**

- ማዳመጥ እና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መጻፍ

## ማዳመጥ

# አረንጓዴ ተክሎች

**መምህር፡**

- የሚቻል ከሆነ በደቡብ ክልል ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ደኖችና እና አረንጓዴ ስፍራዎችን አውንታዊ በሆነ መንገድ የሚያሳይ (ከ2-3 ደቂቃ ያልበለጠ) በድምጽ የታገዘ ቪዲዮ በማዘጋጀት እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ (ከተቻለ ብቻ ነው)፡፡

- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ቀደም ብለው በመምህሩ መምሪያ ላይ ያለውን የፅለቱን ምንባብ ኮፒ በማድረግ ለተማሪው/ዋ በመስጠት በተቀመጡበት በአርምሞ (ድምጽ ሳያሰሙ) እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

- **"አረንጓዴ ተክሎች"** የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎች ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡
- መምህር፤ ምንባቡን በእርጋታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በመጨረሻም ተማሪዎች የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጥያቄዎችን በጽሁፍ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

# አረንጓዴ ተክሎች

አርንጓዴ ተክሎች የምንላቸው በአካባቢያችን በስፋት በቅለው የሚገኙ አረንጓዴ ቅጠል ያላቸውን እጽዋት ነው፡፡ እነዚህ እጽዋቶች በብዛት በሚገኙበት አካባቢ፣አካባቢው በሙሉ ወደ አረንጓዴነት ተለውጦ ማየት የተለመደ ነው፡፡ እነዚህም ተክሎች ከትናንሾቹ እጽዋት ጀምሮ እስከ ተላልቆቹ ድረስ በአረንጓዴተክሎች ስር ይታቀፋሉ፡፡

አረንጓዴ ተክሎች የምንላቸው የመንገድ ዳር ዛፎች፣ የጫካ ደኖች፣ የጌጥ አበባዎች፣ የፍራፍሬ ተክሎች፣ወዘተ. ይካተቱባቸዋል፡፡ እነዚህ አረንጓዴ ተክሎች የተለያየ ጠቀሜታ ያላቸው ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ ለምግብነት፣ ለማገዶ እንጨትነት፣ ለቤት መስሪያነት፣ የሚያገለግሉ መሆናቸውን ማወቅ ይቻላል፡፡ ከዚህም በላይ አረንጓዴ ተክሎች ለሰው ልጅ ህይወትና ለአካባቢ አየር ንብረት መስተካከል ወሳኝነት አላቸው፡፡

አረንጓዴ ተክሎች በቅጠሎቻቸው አማካኝነት ምግባቸውን ይሰራሉ፡፡ በተጨማሪም ኦክስጂንን አምርተው ወደ ከባቢ አየር ይለቃሉ፡፡ ሰዎች ይህንን ኦክስጂን ተቀብለው በምትኩ ካርበን ዳይ ኦክሳይድ ይለቃሉ፡፡ የሰው ልጅም ለመኖር ኦክስጂን ያስፈልገዋል፡፡ ተክሎችም ካረበን ዳይ ኦክሳይድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ስለዚህ ሁለቱም ተሳስረው ይኖራሉ፡፡ በተጨማሪም አረንጓዴ ተክሎች የዝናብ እጥረት እንዳይከሰትና ምድራችን ወደ በረሃማነት እንዳትቀየር ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

**መምህር፡**

- በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በማሰራት የተማሪዎቹን አዳምጦ የመረዳት ደረጃ ይፈትሹ፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- **"አረንጓዴ ተክሎች"** በሚል ርዕስ ለማዳመጥ ክሂል የቀረበላቸውን ምንባብ በእርጋታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ቀደም ብለው በመምህሩ መምሪያ ላይ ያለውን የዕለቱን ምንባብ ኮፒ በማድረግ ለተማሪው/ዋ በመስጠት በተቀመጡበት በአርምሞ እንዲያነቡ እና ጥያቄዎችን እዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺዎችን እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች በተሰጣቸው ቃላት ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ምሳሌ በመስጠት ያግዟቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ምላሾቻቸውንም ይቀበሏቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን በመጠቀም ስለቃላት ፍች ያላቸውን ግንዛቤ እንዲናገሩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያበረታቷቸው፡፡

ምሳሌ፡- - የቃላት ፍች ማለት ምን ማለት ነው?

ቃላትን ጻፉ፡፡)

- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ጥያቄዎችን በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ተማሪው/ዋ በጽሁፍ እንዲመልስ/ድትመልስ ያበረታቷቸው፡፡

- የቃላት አውዳዊ እና ፍካሬያዊ ፍች ምንነትን በተመለከተ የቀረበውን ማስታወሻ ይጻፉላቸው።
- የቃላት አውዳዊ፣ እማሬያዊና እና ፍካሬያዊ ፍችን በተመለከተ የቀረበውን ማስታወሻ እንደክፍል ደረጃቸው ያብራሩላቸው በምሳሌዎችም ደጋግመው ያስሯቸው።
- ተማሪዎች ልምምድ እዲያደርጉ የተለያዩ ቃላትን በመስጠት ያግዟቸው።

**የቃላት አውዳዊ ፍች**

የቃላት አውዳዊ ፍች የምንለው አንድ ቃል በተለያዩ ዓረፍ ተነገሮች ውስጥ በመግባት የሚሰጠውን ትርጉም ሲሆን የአንድ ቃል ትክክለኛ ፍች የሚታወቀዉም ቃሉ ከሌሎች ቃላት ጋር በመሆን መልዕክት ማስተላለፍ ሲችል ነው። **ምሳሌ፦**

1. አቤል ትምህርት ቤት በሰዓቱ <u>ደረሰ</u>።  መጣ/በቦታው ተገኘ
2. ደራሲው መጽሀፍ <u>ደረሰ</u>።  ጻፈ

**የቃላት እማሬያዊ ፍች**

የቃላት  እማሬያዊ ፍች ማለት ቀጥተኛ ወይም ከመዝገበ ቃላት የሚገኝ ፍች ማለት ነው። **ምሳሌ፦**

1. **<u>በግ</u>**  ሣር ተመጋቢ የቤት እንስሳ
2. **<u>ርግብ</u>**  የወፍ ዝርያ

**የቃላት ፍካሬያዊ ፍች**

የቃላት ፍካሬያዊ ፍች ማለት አንድ ቃል ከቀጥተኛ ፍችው በተጨማሪ የሚሰጠው ትርጉም ነው።

ምሳሌ፡-

| ቃል | ቀጥተኛ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|
| እርግብ | በራሪ አዕዋፍ | የዋህ |

**መምህር፡**

- የቃላት አውዳዊ እና ፍካሬያዊ ፍች ምንነትን በተመለከተ ተማሪዎች የተረዱትን እንዲያብራሩ ያበረታቷቸው፤ በመቀጠል ክለሳ ያድርጉላቸው፡፡
- የቃላት አውዳዊ እና ፍካሬያዊ ፍችን በተመለከተ የቀረበውን መልመጃ ያሰሯቸው፤ በሚሰሩበትም ጊዜ ተጨማሪ ምሳሌዎችን በመስጠት ያግዟቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ አይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሰሯቸው የቃላት አውዳዊ እና ፍካሬያዊ ፍቺ እርማት ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

**ሀ. በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት የዓውዳዊ ፍች መልሶች፡፡**

1. አጠራቀመ
2. ጠፋበት
3. ተጎሳቆለ
4. ተረበሸ
5. ቆሸ

**ለ. ለቃላት ቀጥተኛ እና ፍካሬያዊ ፍች መልሶች፡፡**

| ተ.ቁ | ቃል | ቀጥተኛ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|---|
| 1 | አንበሳ | የዱር እንስሳ | ጠንካራ/ጀግና/ጎበዝ |
| 2 | ምላጭ | ከብረት የተሰራ ለጸጉር መላጫ የሚያገለግል | ብልጥ/ጮሌ |
| 3 | እባብ | በደረቱ የሚሳብ ተናዳፊ | ተንኮለኛ/መሰሪ |
| 4 | ቆቅ | በራሪ የወፍ ዝርያ | ንቁ |
| 5 | መሰላል | መወጣጫ | ረጅም |
| 6 | በግ | ሳር በል የቤት እንስሳ | የዋህ/ሞኝ |

**መምህር፡**

- የዕለቱን ትምህርት ከመጀመርዎ በፊት ለተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ምሳሌ፡- መምህር፡- (አንድ ተማሪ ያስነሱና) ስንተኛ መውጣት ትፈልጋለህ/ጊያለሽ?

ተማሪ፡- 1ኛ መውጣት እፈልጋለሁ፡፡

መምህር፡- ጎበዝ፤ ታዲያ 1ኛ ለመውጣት ምን ማድረግ አለብህ/ሽ?

ተማሪ፡- ሁል ጊዜ ማጥናት፡፡

መምህር፡- በጣም ጎበዝ፤ ሁለቱን ዐረፍተ ነገሮች በአንድ ላይ ንገረኝ/ሪኝ?

ተማሪ፡- 1ኛ መውጣት ስለምፈልግ ሁልጊዜ አጠናለሁ፡፡

መምህር፡- እጅግ በጣም ጎበዝ አሁን የነገርከን/ሽን ዓረፍተነገር መስተዋድድ በመጠቀም ነው፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎች እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

- መስተጻምርን በተመለከተ የቀረበውን ማስታወሻ ይጻፉላቸው፡፡

- መስተጻምርን በተመለከተ የቀረበውን ማስታወሻ እንደክፍል ደረጃቸው ያብራሩላቸው

## ማስታዎሻ

## መስተዋድድ

መስተዋድዶች ለብቻቸው ትርጉም መስጠት የማይችሉ ነገር ግን ቃልን ከቃል የማጣመር ተግባር ያላቸው ሆሄ ወይንም የሆሄያት ስብስብ ሲሆኑ በቋንቋ ውስጥም ቁጥራቸው አነስተኛ ነው፡፡

**ምሳሌ**፡- እና ፣ ወይም ፣ ስለ ፣ በ ፣ ከ፣ እስከ

## የመስተዋድድ ዓይነቶች

## በመስተዋድድ ስር መስተጻምሮች ይገኛሉ እነዚህም

መተጻምሮች በሁለት ይከፈላሉ፡፡ - 1. ወደረኛ መስተጻምር እና

2. ጥገኛ መስተጻምር ናቸው፡፡

1. **ወደረኛ መስተጻምር፡-** በዚህ ክፍል ስር የሚገኙ መስተጻምሮች ተመሳሳይ እና ተመጣጣኝ የሆኑ ነገሮችን ወይም ድርጊቶችን የሚያጣምሩ ናቸው፡፡ እነዚህም ( እና (እና) ወይም ናቸው)

ምሳሌ፡-

| ቃላት | ቃላት | ቃላት |
|---|---|---|
| እህት እና ወንድም | ወፍራም እና ቀጭን | መሸጥ ወይም መግዛት |
| ሽንኩርት ወይም ድንች | ዘመናዊ እና ባህላዊ | ሰራ እና አገኘ |
| ወተት እና ሻይ | ደግ ወይም ክፉ | መታ እና ሄደ |

ከላይ የተሰጠው ሰንጠረዥ እንደሚያሳየን ወደረኛ መስተጻምር የሚባሉት ስም እና ስም ፣ ቅጽል እና ቅጽል፣ ግስ እና ግስን ወዘተ (ቃላትን እርስ በእርስ) የሚያጣምሩ ናቸው፡፡

2. **ጥገኛ መስተጻምር፡** የሚባሉት አንድ ግስ በሌላ ግስ ላይ ጥገኛ ሆኖ እንዲገባ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- **ስለ**ሚያስላት መታከም አለባት

ጠንክሮ **በ**መነገዱ አተረፈ

**ከ**መጣ አይሄድም

## ሰዋስው

**መምህር፡**

- መስተጻምርን በተመለከተ ተማሪዎች የተረዱትን እንዲመልሱ ጥያቄዎን ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው።
- ተማሪዎች በጥንድ ወይንም በቡድን (ከ4 ተማሪዎች ባልበለጠ) ሆነው መስተጻምሮችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰረቱ እና ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጉ።
- መስተጻምርን በተመለከተ የቀረበላቸውን ጥያቄዎች በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያድሩ ።
- ተማሪዎች በጥንድ ወይንም በቡድን ሆነው መስተጻምሮችን ከዓረፍተነገሮችን ውስጥ እንዲለዩ ያድርጉ።
- ተማሪዎች ለሰሯቸው ጥያቄዎች እርማት ይስጧቸው።
- በክፍል ውስጥ አይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያበረታቷቸው።

### ለ. ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መልሶች።

1. ደረቅ
2. መንቀል
3. ጉዳት
4. መመለስ
5. ተቀባይ
6. ቅዝቃዜ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች በጥንድ ወይንም በቡድን (4/6 ተማሪዎች ባልበለጠ )ሆነው መስተጻምሮችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ምሳሌዎችን በመጻፍ እና ገለጻ በማድረግ ያግዟቸው፡፡

- ተማሪዎች በጥንድ ወይንም በቡድን ሆነው መስተጻምሮችን በመጠቀም የጻፏዋቸውን ዓረፍተነገሮች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያበረታቷቸው፡፡

## ንባብ

## ሎረንሶና እኒቾ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ለብቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከቤተሰብ ወዘተ ጋር በመሆን ለአካባቢያቸው የሚጠቅም ምን ተግባራትን አከናውነው እንደሚያውቁ ይጠይቋቸው፡፡ መልሶቻቸውንም ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- በተማሪ መጽሐፍ ላይ ሎረንሶና እና እኒቾ በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት ቀደምት ዕውቀታቸውን በመጠቀም የቅድመ ንበባ ጥያቄዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ሎረንሶ እና እኒቾ በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች የምንባቡን መልዕክት እዲናገሩ ያበራታቷቸው፡፡
- በመጨረሻም ተማሪዎች ለክፍል ጓደኞቻቸው በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ተራበተራ (አንቀጾችን በመቀባበል) እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

## ጽህፈት

**መምህር፡**

- ጀሚላና እና ሎሚ በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን የድህረ ንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡

- ጀሚላና ሎሚ በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ዋና መልዕክት በራሳቸው አገላለጽ በአራት አረፍተ ነገር እንዲጽፉ ያግዟቸው፡ የጻፉትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- ጀሚላና ሎሚ በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ውስጥ ሌሎች ቃላትን በመጠቀም እና አገባባዊ ፍቻቸውን በመጻፍ እና ገለጻ በማድረግ በምሳሌ ያስረዷቸው፡፡

### ሐ. ለቃላቱ የተሰጡ ተመሳሳይ ፍቾች መልሶች፡፡

1. ምሳሌ/አብነት
2. ማከማቸት/ማጠራቀም
3. ማሳመር/ማስጌጥ
4. ዋና /ትልቅ፣ ከፍታ
5. ቦታ/መገኛ
6. ማጠናቀቂያ/መጨረሻ
7. ተቀያየሩ
8. በሥርዓቱ

## ሰዋስው

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎች ስለዓረፍተነገር ምንነት የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
  - ዓረፍተነገር ማለት ምን ማለት ነው?
  - የምትፈልጉትን ሃሳብ በዓረፍተነገር ግለጹ?

ለምሳሌ፡- መምህር፡- ለሀገራችሁ ምን ማበርከት ትፈልጋላችሁ?

ተማሪ፡- እኔ ሀኪም ሆኜ የታመሙ ሰዎችን ማከም እፈልጋለሁ፡፡

መምህር፡- በጣም ጥሩ ይህ ዓረፍተ ነገር ይባላል፡፡ (ሌሎቻችሁም ስለራሳችሁ ፍላጎት ተናገሩ፡፡)

- ❖ ዓረፍተነገርን በተመለከተ የቀረበላቸውን ማስታወሻ በደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡ ያድርጉ፡፡
- ❖ የዓረፍተነገርን ምንነት በተመለከተ የቀረበውን ማስታወሻ እንደክፍል ደረጃቸው ያብራሩላቸው በምሳሌዎችም ደጋግመው ያስሯቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ ዓረፍተ ነገር መሆኑን ወይንም አለመሆኑን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡

**መምህር**

- ❖ ተማሪዎች ስለዓረፍተነገር ዓይነቶች የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ የዓረፍተነገር ዓይነቶችን በተመለከተ የቀረበላቸውን ማስታወሻ በደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡ ያድርጉ፡፡

**ውስብስብ ዓረፍተነገር፡-** ውስብስብ ዓረፍተ ነገር የምንለው ሁለትና ከዛ በላይ ግሶችን (ማሰሪያ አንቀፆችን) የሚይዝ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** ሀ. ፀሀይ የወጣ ይመስላል፤ ይሁን እንጂ ዝናብ መዝነቡ አይቀርም፡፡

ለ. በሚገባ ማጥናት አለብን ፤ አለበለዚያ ጥሩ ውጤት አናመጣም፡፡

. ሐ. ዕውቀት ሊኖረንኝ ይገባል፤ ስለዚህ መማር አለብኝ፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን (ከ4 ተማሪዎች ባልበለጠ) እንዲቀመጡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች የተሰጧቸውን ጥያቄዎች በሚያከናውኑበት ወቅት ምሳሌዎችን በመስጠት ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ስለመስተጻምር ተማሪዎች ቀድመው የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን በመጠቅ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን (ከ4/6 ተማሪዎች) ባልበለጠ እንዲቀመጡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች የተሰጧቸውን ወደረኛ መስተጻምሮችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ ጥያቄዎች በሚያከናውኑበት ወቅት ምሳሌዎችን በመስጠት ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ለተማሪዎች ስለአያያዥ ቃላት ክለሳ በማድረግ የተረዱትን እንዲያስታውሱና እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተነገር እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

መምህር

ተማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የምዕራፉን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ መረዳታቸው በተማሪዎች መጽሀፍ ላይ የተቀመጡትን የምዕራፉን ማጠቃለያ ጥያቄዎች እንዲሰሩ በማደረግ ያረጋግረጡ፤ እንዲሁም ከምዕራፉ ይዘት ጋር የሚገናኙ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመስጠት የምዕራፉን ትምህርት ያጠቃሉ፡፡

- ✓ በዚህ ምዕራፍ ስር አዳምጦ እና አንብቦ የመረዳትን፣ የመናገር እና የመጻፍ ክሂሎችን አዳብረዋል፡፡
- ✓ የቃላት አውዳዊ እና ፍካሬያዊ ፍቺ ምነትን እና አጠቃቀምን የተመለከተ በቂ ዕውቀት አግኝተዋል፡፡
- ✓ የመስተጻምር ምንነትን እና ዓይነቶችን፤ የዓረፍተነገር ምንነትን እና ዓይነቶችን እንዲሁም የአያያዥ ቃላት ምንነትን ለይተው አውቀዋል፡፡
- ✓ ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍቺን ሰጥተዋል፡፡
- ✓ ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን በመለየት አሳይተዋልል፡፡
- ✓ መስተጻምሮችን እንዲሁም አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተነገሮችነ ጽፈዋል፡፡
- ✓ ካዳመጧቸው እና ካነበቧቸው ንባብ ውስጥ በራሳችሁ አገላለጽ ሃሳቦችን ጽፈዋል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት (፪)

# የመንገድ ደህንነት

**የተሰጠ ክፍለ ጊዜ 9**

**ከዚህ ምዕራፍ መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች:-**

- የመንገድ ላይ ጥንቃቄ የሚለውን ምንባብ ያዳምጣሉ፡፡
- የትራፊክ አደጋ የሚደርስበትን መንገድ ያብራራሉ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራን ፍች ይሰጣሉ፡፡
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው ዓረፍተነገር ይመስርታሉ፡፡

**የትምህርቱ ይዘት:-**

ማዳመጥ እና መናገር

ማንበብ

ቃላት

መጻፍ



## ማዳመጥ

## "የመንገድ ላይ ጥንቃቄ"

**መምህር፡**

- "የመንገድ ላይ ጥንቃቄ"የሚለውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጉ፡

  እባኮትን መምህር ከዚህ በመቀጠል ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡ በመቀጠልም ማስታወሻም እንዲይዙም ይንገሯቸው፡፡በመጨረሻም ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ምላሽ በሚሰጡ ጊዜ ያበረታቷቸው፡፡የድህረ ንባብ ጥያቄዎችንም ያሰሩ፡፡

## የመንገድ ላይ ጥንቃቄ

በኢትዮጵያ በተለያዩ አከባቢዎች አሳሳቢ በሆነ ደረጃ የመንገድ ለይ አደጋዎች ይደርሳሉ። በዚህም በየዓመቱ ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን ያጣሉ።አያሌ ሰዎች የአካል ጉዳተኛ ይሆናሉ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል አብዛኛዎቹ እግረኞች ናቸው።የመኪና አደጋ የሚደርስባቸው ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው ነው።ይህንን አሳሳቢ አደጋ ለመቀነስ የመንገድ አጠቃቀም ሥርዓትን መከተል ያስፈልጋል።እግረኞች በመኪና መንገድ ላይ ሲሄዱ ወይም ሲያቋርጡ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል።

ተሽከርካሪዎች በሚበዙባቸው አካባቢዎች ለመጓዝ በእግረኞች የሚደረጉ ጥንቃቄዎች አሉ። በመጀመሪያ እግረኞች ለእግረኞች ተብሎ በተዘጋጀ መንገድ ካለ በዚያ መጠቀም ይኖርባቸዋል። የእግረኞች መንገድ ከሌለ ግን ሁለተኛውን አማራጭ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዞ መጓዝ ነው።ይህም የሚመረጠው ከፊት ለፊት የሚመጣውን መኪና በትኩረት ለማየት ስለሚያስችል ነው።ይህ ዓይነቱ ጥንቃቄ የመኪኖችን አመጣጥ በንቃት ለመከታተል ያስችላል።

የመኪና መንገድ ለማቋረጥ የሚወሰዱ ጥንቃቄዎች አሉ።በመጀመሪያ ለእግረኛ ተብሎ ነጭ ቀለም የተቀባ ቦታ (ዜብራ) ካለ ማየት ያስፈልጋል።በመቀጠልም ማቋረጫው መኖሩ ከተረጋገጠ መኪኖች ለእግረኞች ቅድሚያ ሰጥተው መቆማቸውን ማረጋገጥ ይገባል።ከዚያም መንገዱን ማቋረጥ ይቻላል።

የትራፊክ መብራት ባለበት ቦታ ቀዩ መብራት በርቶ መኪኖችን ሲያስቆም ማቋረጥ ተገቢ ነው። ሆኖም የትራፊኩ መብራት ቢጫ በሚበራበት ጊዜ አንዳንድ መኪኖች ሊንቀሳቀሱ ስለሚችሉና መብራት ሙሉ በሙሉ አረንጓደ ሲበራ በፍጥነት ስለሚበሩ እግረኞች ማቋረጥ የለባቸውም። የመኪና መንገድ ለማቋረጥ ሌላው አማራጭ ደግሞ በትራፊክ ፖሊስ በመታገዝ ማቋረጥ ነው። በአጠቃላይ ውድ ህይወትንና ክቡር አካልን ላለማጣት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም በእግረኛ መንገድ ወይም ግራ ጠርዝን ይዞ መጓዝ ይገባል። የመንገድን ግራና ቀኝ በመቃኘት እና በቅርብ መኪና አለመኖሩን አረጋግጦ ማቋረጥም ተገቢ ነው።

(ብሔራዊ የመንገድ ደህንነት አስተባባሪ ጽ/ቤት።1996። ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ለማዳበር የተዘጋጀ መማሪያ (ማጣቀሻ አጋዥ መጽሐፍ) ካሪኩለም ጋይድ ገጽ 28-30 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

**መምህር፡**

❖ በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተሰጡትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በማሰራት የተማሪዎችን አዳምጦ የመረዳት ደረጃ ይፈትሹ ፤እርማት ይስጧቸው፡፡

❖ ባዳመጡት ምንባብ መሰረት ለቃላት ተመሳሳይ ፍች እንዲሰጡ ያድርጉ፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

### ለ. የቃላት ቀጥተኛ ፍች፡፡

1 በመኪና የማይሄዱ.

2 .ብዙ

3. መከልከል

4 .መሻገር

5 ማስተዋል.

6 .በንቃት



## ጽህፈት

**መምህር፡**

የመንገድ ለይ ጥንቃቄ በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ላይ ባዳመጡት መሰረት የተረዱትን ሀሳብ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም በተሰጣቸው የአቅጣጫ መጠቆሚያ መሰረት ፊደላትን ወደ ጎንና ወደታች በመልስ መስጫ ሳጥን ውስጥ በትክክል መጻፋቸውን ይከታተሉ፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍች የሚያውቁትን እንዲመልሱ ይጠይቋቸው/ያበረታቷቸው፡፡

ምሳሌ፡- በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለውን የመጻፊያ ሰሌዳ ቀለም እንዲናገሩ ያድርጉ፤ በመቀጠል የጠሩትን ቀለም ተቃራኒ እንዲጠሩ ያድርጉ፤

ጥቁር ≠ ነጭ

ነጭ ≠ ጥቁር

**መምህር፡**

- መምህር የብርጭቆ ወረቀት በተወሰነ መጠን ቆርጠው በማዘጋጀት ተማሪዎች በሁለቱም መልኮች ተራበተራ እንዲዳስሱ በማድረግ የተሰማቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ፤ በመቀጠል የምላሻቸውን ተቃራኒ ቃል እንዲጠሩ ያድርጉ፤

ለስላሳ ≠ ሻካራ

ሻካራ ≠ ለስላሳ

- ተመሳሳይ ቃላትን ለማስተማር፡-

ምሳሌ፡-

በጥቁር ሰሌዳ ላይ **እኔ ቁርሴን** **<u>በላሁ</u>**፡፡ የሚል አረፍተነገር በመጻፍ ግሱ ላይ ያስምሩበት እና ያንብቡላቸው፤ በመቀጠልም ተማሪዎች የተሰመረበትን ቃል በተመሳሳይ ቃል በመተካት ዓረፍተነገሩን በድጋሚ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

- ተማሪዎች **እኔ ቁርሴን ተመገብኩ**፡፡ ብለው "ሲመልሱ" በላሁ ለሚለው ቃል ተመሳሳዩ ተመገብኩ መሆኑን ያስረዷቸው፡፡
- ስለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍች ምንነት የተዘጋጀውን ማስታወሻ ይጻፉላቸው፡፡
- ስለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍች ምንነት የቀረበውን ማስታወሻ እንደክፍል ደረጃቸው ያብራሩላቸው በምሳሌዎችም ደጋግመው ያሰሯቸው፡፡

❖ተማሪዎች ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ለመስጠት የተዘጋጁትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**ቃል** :_ ማለት የፊደላት ስብስብ ነው፡፡

ምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| ሰመላል | ቃል አይደለም ምክንያቱም ፊደሎቹ በስርዓት ስላልተደረደሩ ትርጉም አይሰጥም፤ |
| መሰላል | ቃል ነው፤ ምክንያቱም ፊደሎቹ በስርዓት ስለተደረደሩ ትርጉም ይሰጣል፡፡ |

**የቃላት ተመሳሳይ ፍችː-** እርስ በእርስ **ተደጋጋፊ** የሆነ ሃሳብን የሚይዙ ቃላት ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- ወረፋ = ተራ

መዞር = መሽከርከር

**የቃላት ተቃራኒ ፍችː-** እርስ በእርስ **አፍራሽ** የሆነ ሃሳብን የሚይዙ ቃላት ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- መጣ = ሄደ

ወፍራም = ቀጭን

**መምህር፡**

- ተማሪዎች የሰንጠረዥ ጥያቄውን በደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡ ያድርጉ፡
- ተማሪዎችን በጥንድ ወይንም በቡድን (ከ4/6 ተማሪዎች ባልበለጠ) እዲቀመጡ ያድርጉ፡
- በተዘጋጀው ጥያቄ መሰረት ተመሳሳይ ምሳሌዎችን ያለማምዷቸው፡፡
- ተማሪዎች የቃላት ጨዋታውን ከመጀመራቸው በፊት የተሰጡትን ፍንጮች እና ሕጎች እንዲረዱ ያግዟቸው፡፡

1. በአንድ ሳጥን ውስጥ ከአንድ ፊደል በላይ መጻፍ አይቻልም፡፡
2. መልሶቹ የሚቀመጡት በታዘዘው አቅጣጫ (ወደ ጎን ወይንም ወደ ታች) ብቻ ነው፡፡
3. የተሸፈኑ ሳጥኖች ውስጥ ምንም ዓይነት ፊደል ማስቀመጥ አይቻልም፡፡
4. መልሶቹን ቁጥሮቹ አጠገብ የተቀመጡትን ፊደሎች እንደ መነሻ ይጠቀሙ፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች የተዘጋጁትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ድጋፍም ያድርጉላቸው፤
- ለመልሶቻቸውም እርማት ይስጧቸው፡፡

## ጽሕፈት

**የአቅጣጫ መጠቆሚያ መልስ**


| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 ጀ | 2 ግ | ና | 4 አ | 5 ክ | 10 ሱ | ም | | |
| | 3 ን | ብ | ክ | ራ | ሪ | 8 ሳ | 6 ሙ | ና |
| | በ | | 7 ስ | ር | | | ቀ | |
| | ኛ | | 9 ት | ራ | ስ | | ጫ | |

**ወደ ጎን መልሶች**

1. ጀግና
3. ንብ
4. አክሱም
7. ስር
8. ሳሙና
9. ትራስ

**ወደ ታች መልሶች**

2. ግንበኛ
4. አክስት
5. ክራር
6. ሙቀጫ
10. ሱሪ



## ንባብ

## የሾፌሩ ታሪክ

**መምህር፡**

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ "**የሾፌሩ ታሪክ**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት የቀደመ ዕውቀታቸውን በመቀስቀስ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን አንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- "**የሾፌሩ ታሪክ**" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ተራበተራ ለክፍል ጓደኞቻቸው ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ አንቀጾችን እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ በሚያነቡበትም ጊዜ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- "**የሾፌሩ ታሪክ**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በድጋሚ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች የምንባቡን መልዕክት እዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለድህረ ንባብ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፤ (መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በጽሁፍ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡)

## ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለተመሳሳይ እና ተቃራኒ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

## መናገር

**መምህር፡**

- ተማሪዎች በጥንድ ወይንም በቡድን (ከ4/6 ተማሪ ባልበለጠ) በማድረግ በቡድን እንዲቀመጡ ያድርጉ፤
- በክፍል ውስጥ እንዳለው የቡድን ብዛት የመወያያ ጥያቄዎችን ያዘጋጁ፤

ምሳሌ፡-

ለቡድን አንድ ፡- የትራፊክ እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት ነው?

ለቡድን ሁለት፡- የትራፊክ አደጋ መንስኤዎች ምን ምን ናቸው?

ለቡድን ሶስት፡- የትራፊክ አደጋን እንዴት መከላከል ይቻላል?

ለቡድን አራት፡- የምታውቁትን የእግረኛ የመንገድ አጠቃቀም ሕጎችን ዘርዝሩ?

- ተማሪዎች በቡድናቸው ሆነው የሚደርሳቸውን የመወያያ ጥያቄ እንዲሰሩ ያድርጉ፤ በሚሰሩበት ጊዜ አንድ ተወካይ በመምረጥ ሀሳባቸውን /ምላሾቻቸውን በማስታወሻ ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ፤
- ውይይታቸውን በሚሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ካጠናቀቁ በኋላ በጥያቄዎቹ ቅደም ተከተል መሰረት በተወካይ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻቸው ጽብረቃ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡ ሌሎች ቡድኖችም ከሚቀርበው ምላሽ የተማሩትን ዋና ዋና ሃሳብ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡**

- በተማሪዎች መጽሀፍ ላይ "**አንበሳ**" በሚል ርዕስ ላይ የቀረበውን አንቀጽ (ምንባብ) ተማሪዎች በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) በተናጠል በመደጋገም እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- በዚህ አቀላጥፎ የማንበብ ደረጃ ላይ ተማሪዎች **ከትክክለኛነት፣ ከፍጥነት** እና **ከድምጸት** ደረጃዎች መካከል በዚህ ንባብ ላይ **ትክክለኛነትን** ብቻ ማሳካታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በቅድሚያ ግን ስለ አቀላጥፎ ማንበብ ማስታዎሻ ይስጧቸው፡፡

**ማስታዎሻ**

አቀላጥፎ ማንበብ ማለት ለክፍል ደረጃው በተወሰነ ፍጥነት፣ ትክለኛነትና አገላለጽ ማንበብ ወይም መግለጽ ማለት ነው፡፡

**መምህር፡**


- ተማሪዎች "**አንበሳ**" የሚለውን ንባብ ከማንበባቸው በፊት እርስዎ በተመጠነ የድምጽ ደረጃ በቅልጥፍና በማንበብ ምሳሌ አሳዩአቸው፤
- ተማሪዎች በተለማመዱት መሰረት "**አንበሳ**" በሚል ርዕስ የቀረበውን አንቀጽ (ምንባብ) ተራበተራ ከተማሪዎች ፊት ቆመው እንዲያነቡ ያድርጉ፤
- በሚያነቡበትም ጊዜ እርስዎ ሰዓት (ደቂቃ በመያዝ) ተማሪዎች በጽሁፉ ውስጥ ያሉትን ቃላት በክፍል ደረጃቸው ልክ በሚገባ የፍጥነት ደረጃ እያነበቡ ስለመሆናቸው ማስታወሻዎችን በመያዝ ያበረታቷቸው፤ የተማሪዎችዎንም የንባብ ደረጃ ይፈትሹ፤
- የሚቻል ከሆነ በክፍል ውስጥ ዓይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ ስለአንበሳ አካላዊ ቅርጽ እና አኗኗር ያዳመጡትን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- በቅድሚያ በኤ1 (የግራፍ መስሪያ) ወረቀት ላይ አራት ኪሶችን ያዘጋጁ፤ (ሻሽ ቦርድን ይጠቀሙ) በመቀጠል፡-
  - ታታሪ
  - ትጉህ
  - ጠንካራ ፣ ብርቱ እና
  - ጎበዝ የሚሉ ቃላትን ለየብቻ በሌላ ጠንካራ ወረቀት (ካርቶን ላይ ጽፈው ያዘጋጁ)
- በማእከላዊ ኪስ ዙሪያ ባሉት ኪሶች ውስጥ "ታታሪ፣ ትጉህ፣ ጠንካራ እና ብርቱ" የሚሉትን ቃላት እንዲታዩ አድርገው በማስቀመጥ ተማሪዎች ለነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ቃል እንዲፈልጉ ያድርጉ፤ ለሚሰጡትም ምላሽ ትክክል ሲሆኑ ቃሉን በማዕከላዊ ኪስ ውስጥ በሚታይ መልኩ ያስቀምጡ፡፡

ምሳሌ፡-




- ተማሪዎች በሳጥኑ ዙሪያ ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳይ የሚሆነውን ቃል ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ በመምረጥ በክፍት ቦታው ላይ እንዲጽፉ የድርጉ፡፡
- ተማሪዎች በምሳሌው መሰረት እንዲሰሩ ያግዟቸው፤
- በክፍል ውስጥ ዓይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል ያሰሯቸው፤
- ለጥያቄዎቹም እርማት ይስጧቸው፤

## ሰዋስው

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለአያያዥ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያድርጉ፤
- አያየዥ ቃላትን በተመለከተ የተዘጋጀውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም ለመልሶቻቸውም እርማት ይስጡ፡፡

**ሀ. በተዘረዘሩት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በመግባት ሃሳቦችን ሊያሟሉ የሚችሉ አያያዥ ቃላት መልሶች፡፡**

1. ሐ 2. ሀ 3. ለ 4. መ 5. ሀ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓረፍተ ነገር የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያድርጉ፤
- ተማሪዎች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የዓረፍተነገሮቹን ሃሳብ የተሟላ እንዲሆን በምሳሌ ያሳዩአቸው፡፡
- ተማሪዎች የተዘጋጀውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያድርጉ፤ በሚሰሩበት ጊዜ ድጋፍ ያድርጉላቸው፤ በመጨረሻም ለመልሶቻቸው እርማት ይስጧቸው

## ጽህፈት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለተራ እና ውስብስብ ዓረፍተነገሮች የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያድርጉ፤
- ተማሪዎች ከተሰጠው አንቀፅ ውስጥ ውስብስብ ዓረፍተነገሮቹን በመለየት እንዲጽፉ ያድርጉ፤
- ተማሪዎች በሚሰሩበት ጊዜ ድጋፍ ያድርጉላቸው፤ በመጨረሻም ለመልሶቻቸው እርማት ይስጧቸው፡፡

### ሀ. ከጽሁፉ ውስጥ የወጡ ውስብስብ ዓፍተነገሮች መልሶች፡፡

1. በከተማዋ ስለመንገድ ደህንነት በተመለከተ በተለያየ መንገድ ትምህርት ይሰጣል፤ ይሁን እንጂ በርካታ የትራፊክ አደጋዎች ያጋጥማሉ፡፡
2. ምክንያቱም የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ለምፍጠር ባለድርሻ አካላት ሁሉን አቀፍ ጥረት እያረጉ ይገኛሉ፤ ቢሆንም ህብረተሰቡ የግንዛቤ ለውጥ አላመጣም፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ዓረፍተነገሮች የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያድርጉ፤
- ተማሪዎች የተለያዩ ሃሳቦችን በአረፍተነገር እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡

  ምሳሌ፡- - ዛሬ ምን አደረጋችሁ?

  - አሁን ምን ትምህርት እየተማራችሁ ነው?

  - ተማሪዎች ተዘበራርቀው የተጣቸውን ቃላትየተሟላ ሃሳብ እንዲሰጥ አድርገው በስርዓት እንዲደረድሩ ያድርጉ፡፡
  - ተማሪዎች በሚሰሩበት ጊዜ ድጋፍ ያድርጉላቸው፤ በመጨረሻም ለመልሶቻቸው እርማት ይስጧቸው

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለመስተዋድድ እና ስለዓረፍተነገሮች የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያበረታቷቸው፡፡
  - ተማሪዎች አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተ ገሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

*መምህር*

*ተማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የምዕራፉን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ መረዳታቸው በተማሪዎች መጽሀፍ ላይ የተቀመጡትን የምዕራፉን ማጠቃለያ ጥያቄዎች እንዲሰሩ በማደረግ የምዕራፉን ትምህርት ያጠቃሉ፡፡*

- ✓ በዚህ ምዕራፍ ስር አዳምጦ እና አንብቦ የመረዳትን፣ የመናገር እና የመጻፍ ክሂሎችን አዳብረዋል፡፡
- ✓ ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍችን ሰጥተዋል፡፡
  ስለመስተዋድድ እና ስለውስብስብ ዓረፍተነገሮች በሚገባ አውቀው መስተዋድዶችን በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን መመስረት ችለዋል፡፡
- ✓ በተሰጣቸው የመወያያ ርዕስ ላይ በመወያየት ሃሳብ የማፍለቅ እና የመናገር ክሂላቸውን አዳብረዋል፤
- ✓ አቀላጥፎ ለማንበብ የሚረዳቸውን ልምምድ በሚገባ አድርገዋል፤
  አያያዥ ቃላትን በመጠቀም የዓረፍተነገሮችን ሀሳብ ማሟላት ችለዋል፡፡
- ✓ ያዳመጧቸው እና ያነበቧቸውን ምንባቦች ሃሳብ በራሳችሁ አገላለጽ ጽፈዋል/ተናግረዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት (፫)

## መረዳዳት

### የተሰጠ ክፍለ ጊዜ 9

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ያዳመጡትን ምንባብ መልዕክት ይናገራሉ፤
- በክፍል ደረጃቸው ያነበቡትን ጽሁፍ ዋና ሃሳብ ይለያሉ፤
- ቅጥያዎችን ተጠቅመው አረፍተነገር ይጽፋሉ፤
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው ነጠላ እና ውስብስብ አረፍተነገር ይመሰርታሉ።

**የትምህርቱ ይዘቶች፡-**

- አዳምጦ ስሜትን ማንጸባረቅ
- በፍጥነት አቀላጥፎ ማንበብ
- በባለ ቅጥያ ቃላት ዓረፍተ ነገር መመስረት
- ተራ እና ውስብስብ ዓ. ነገሮች

 **ማዳመጥ**

## እህትማማቾቹ

**መምህር፡**

- **"እህትማማቾቹ"** የሚለውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲመልሱ ያበረታቷቸው።
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ያበረታቷቸው።
- ምንባቡን በእርጋታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው።
- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ቀድመው ምንባቡን ኮፒ አድርጎ በመስጠት እንዲያነቡ ያድርጉ።
- ተማሪዎች ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ በምገባ እያዳመጡ መሆናቸው የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያረጋግጡ ።
- ተማሪዎች የተዘጋጀውን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፤

## እህትማማቾቹ

ጀሚላ እና ሎሚ ይባላሉ፡፡ የሚኖሩት በሀላባ ከተማ ዉስጥ ነው፡፡ ሁለቱም በእጅጉ ይዋደዳሉ፡፡ ጀሚላ ሎሚ በዕድሜ የምትበልጣት በአራት ዓመት ነው፡፡ ጀሚላ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ሎሚ ደግሞ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ናት፡፡ ዘወትር ወደትምህርት ቤት ሲሄዱም ሆነ ከትምህርት ቤት ሲመለሱ ተለያይተው አያውቁም፡፡ ጀሚላ የራሷን የቤት ሥራ ከጨረሰች በኋላ ሎሚን ታስጠናታለች፡፡ ሎሚ ጀሚላን አቅሟ በፈቀደ ሁሉ በሥራ ታግዛታለች፡፡

በአንድ የእረፍት ቀን ግን ቤተሰቦቻቸው በጠዋት ተነስተው ራቅ ወዳለ ቦታ ዘመድ ለመጠየቅ እንደሚሄዱና ሲመለሱም ከእንግዳ ጋር አብረው እንደሚመጡ ነግረዋቸው ተሰናብተው ወጡ፡፡ ወላጆቻቸው ከሄዱ በኋላ ጀሚላ ምግብ በማብሰል እና የተለያዩ የማዕድ ቤት ሥራዎችን ስትሰራ ዋለች፡፡ ሎሚ ደግሞ የጀሚላ በሥራ መጠመድን በመመልከት ቤቱን ወልዉላ፣ ሶፋውን እና ጠረጴዛዎችን አስተካክላ፣ አልጋውን አንጥፋ፣ ቤቱን ልዩ ዉበት አጎናፀፈችው፡፡

ሀ. ጀሚላና እና ሎሚ ምን ሰሩ?

ለ. ቀጥሎ ምን የሚሆን ይመስላችኋል?

ጀሚላ የማዕድቤቱን ሥራ አጠናቃ ቤቱን ለማስተካከል እየተቻኮለች ወደ ሳሎን ስትገባ ቤቱ እንደመስከረም ሰማይ አምሮ እና ጸድቶ አገኘችው፡፡ ሎሚ የእህቷን መምጣት ስታይ "እህቴ አንቺ ማዕድቤት ሥራ ስትሰሪ እኔ ደግሞ ቤቱን በተቻለኝ አቅም በዚህ መልኩ አዘጋጀሁት፡፡" አለቻት፡፡

ጀሚላ በታናሽ እህቷ አስተውሎትና አሳቢነት በመገረም "አንቺ እኮ እስትንፋሴ ነሽ፤ ቤቱን ሳላዘጋጀዉ እንግዶች ደረሱብኝ ብዬ እየተጨነኩ ነበር፡፡" ብላ ሎሚን ጉንጯን ሳመቻት፡፡ ሁለቱም በጣም ተደሰቱ፡፡ ወዲያውኑ የግቢያቸው በር ተንኳኳና ሎሚ በሩን ለመክፈት በሩጫ ተፈተለከች፡፡ ሲጠበቁ የነበሩ ቤተሰቦቻቸው እና እንግዶችም ወደቤት ገቡ፡፡ ጀሚላ የተዘጋጀውን ምግብ ስታቀራርብ ሎሚ ደግሞ የእጅ ውሃ በማምጣት ወላጆቻቸውን እና እንግዶችን አስታጠበች፡፡ ገበታውም ቀርቦ ከተመገቡ በኋላ እንግዶቹ ስለተደረገላቸው መስተንግዶ አመሰገኑ፤ ወላጆቻቸውም "አንድነትና ትብብራችሁ ሁሌም አብሯችሁ ይኑር" በማለት መረቋቸው፡፡ ጀሚላ እና ሎሚ በመተባበር በሰሩት ሥራ እና ባገኙት ምርቃት እጅግ ተደሰቱ፡፡

### ቃላት

**መምህር፡**

❖ ተማሪዎች ስለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ የሚያውቅትን እንዲመልሱ ይጠይቋቸው/ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

❖ ተማሪዎች ስለቃላት አውዳዊ እና ፍካሬያዊ ፍቺ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡

❖ ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ምሳሌዎችን በመስጠት ያስረዷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ለ. "እህትማማቾቹ" በሚል ርዕስ በቀረቡት ዓረፍተነገሮችውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳይ ፍች መልሶች፡፡

1. አጽድታ
2. በፍጥነት ሮጠች
3. በመደነቅ
4. ካጠናቀቀች
5. እየተጣደፈች

**መምህር፡**

❖ ተማሪዎች **"እህትማማቾቹ"** የሚለውን ምንባብ እንዲያዳምጡ በማድረግ በተመጠነ የድምጽ ደረጃ እና በተገቢው ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡

❖ በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ምንባቡን ኮፒ በማድረግ ይስጧቸው፡፡

❖ ተማሪዎች ካዳመጡት ምንባብ የተረዱትን ሃሳብ በአራት ዓረፍተነገሮች እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ በሚሰሩበትም ጊዜ ያግዟቸው፡፡


## ቃላት

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎች ስለተመሳሳይ እና ተቃራኒ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች በቅድሚያ ለቃላቱ ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- ❖ በክፍል ውስጥ ዓይነስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች በሰጧቸው ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ቃላት ዓረፍተነገሮችን እን ዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

### ሐ. ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍች በመስጠት ዓረፍተ ነገር ለመመስረት የተሰጡ መልሶች፤

| ተ.ቁ | ቃላት | ተመሳሳይ ፍቺ | ተቃራኒ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| 1 | ትልቅ | ግዙፍ | ትንሽ |
| 2 | አጭር | ድንክ | ረጅም |
| 3 | ቆሸሸ | ደፈረሰ | ጠራ |
| 4 | ፈጣን | ቀልጣፋ | ቀርፋፋ |



## ንባብ

### የመረዳዳት ጥግ

**መምህር፡**

- ➢ በተማሪ መጽሐፍ ላይ "**የመረዳዳት ጥግ**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት ቀደምት ዕውቀታቸውን በመጠቀም የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲያከናውኑ/እንዲያብራሩ/ ያበረታቷቸው፡፡
- ➢ "**የመረዳዳት ጥግ**" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

- ተማሪዎች ምንባቡን ካጠናቀቁ በኋላ በራሳቸው አገላለጽ እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡
- ተማሪዎች የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲያከናኑ ያድርጉ፤
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ እርስዎ ያንብቡላቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች አቀላጥፎ የማንበብ ደረጃ ላይ ደረሱ የምንለው 1. **ትክለኛነት** 2. **ፍጥነት** እና 3. **ድምጸት (ስርዓተ-ነጥቦችን በመከተል የጥያቄ፣ የማጋነን...)** ተከትለው ድምጻቸውን እንደ ዓረፍተነገሩ ይዘት በመቀያየር ማንበብ ሲችሉ ነው፡፡ ስለሆነም **በዚህ ክፍለ ጊዜ** ተማሪዎች ቃላትን በሚገባ ወይም **ትክክለኛነትን** ተክትለው እንደዲያነቡ በማድረግ ንባብን እንዲያዳብሩ ያድርጓቸው፡፡
- በተማሪዎች መጽሀፍ ላይ "**የመረዳዳት ጥግ**" በሚል ርዕስ ላይ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳይሰሙ) በተናጠል በመደጋገም እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች በሚሰጣቸው ደቂቃ ውስጥ ከጓደኞቻቸው ፊት በመሆን "**የመረዳዳት ጥግ**" የሚለውን ምንባብ ተራ በተራ አንቀጽ እየተቀባበሉ በትክክል እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ተገቢውን የንባብ ፍጥነት ተከትለው ማንበባቸውን ይከታተሉ፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለተመሳሳይ እና ተቃራኒ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

## ጽህፈት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች **"የመረዳዳት ጥግ"** ከሚለው ምንባብ የተረዱትን ሃሳብ በራሳቸው አገላለጽ እዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡ በሚሰሩበትም ወቅት ይደግፏቸው፤
- የጻፉትን ሃሳብ ተራ በተራ ለክፍል ጓደኞቻው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፤
- ተማሪዎች ስለትምህርትቤታቸው የበጎ አድራጎት ክበብ መረጃ በመሰብሰብ በክፍል ውስጥ ጽብረቃ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡ (በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው)

## ሰዋስው

**መምህር፡**

የሚከተለውን ዓይነት የመነሻ ቅጥያ ብቻ፣ የመድረሻ ቅጥያ ብቻ እና የመነሻና እና የመድረሻ ቅጥያዎችን በአንድነት የሚያሳይ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ያዘጋጁ፤ (ወይም ሻሽ ቦርድን እንደአመቺነቱ ይጠቀሙ)

ምሳሌ፡-

**የቅጥያዎች አጠቃቀም**

| እንደ | ዎች | ስለ | ከ | ኦች |
|---|---|---|---|---|

| የነሻ ቅጥያ | ቃል | የመድረሻ ቅጥያ | ባለቅጥያ ቃል |
|---|---|---|---|
| እንደ- | በላ | | እንደበላ |
| | ቤት | -ኦች | ቤቶች |
| | ማንቆርቆሪያ | | ስለማንቆርቆሪያዎች |

**መምህር፡**

- ተማሪዎች መርጃ መሳሪያውን በመመልከት እየተሳተፉ ቅጥያዎችን ከቃላት ጋር በማጣመር ባለቅጥያ ቃለትን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤
- ስለቅጥያዎች የተዘጋጀውን ማስታወሻ አጽፏቸው፤ እንደ ክፍል ደረጃቸውም በምሳሌዎች ያብራሩላቸው፡፡

## ቅጥያዎች

ቅጥያዎች በዋናው ቃል ላይ በመጨመር ተጨማሪ መረጃን የሚሰጡ ናቸው፡፡ ቅጥያዎች የመነሻ ቅጥያ እና የመድረሻ ቅጥያ በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡

ምሳሌ፡- የመነሻ ቅጥያ

በላ = የመመገብ ድርጊት ፈጸመ

እንደበላ = የመመገብ ድርጊትን እንደፈጸመ/ ወዲያውኑ

ስለበላ = ተመግቦ (በልቶ) ስላጠናቀቀ

አስበላ = የመብላት ድርጊት አስፈጸመ

ሊበላ = የመብላት ድርጊት ሊፈጽም/በዝግጅት ላይ/

ቢበላ = የመመገብ ድርጊት ቢፈጽም/ወደፊት/

የመድረሻ ቅጥያ

ምሳሌ፡-

የመድረሻ ቅጥያ ማለት በቃሉ መጨረሻ ላይ በመጨመር ተጨማሪ መረጃን የሚሰጡ ናቸው፡፡

ቤት + ህ = ቤትህ

ቤት + ሽ = ቤትሽ

ቤት + ኤ = ቤቴ

ቤት + ኣችን = ቤታችን

- የቀረበውን ማስታወሻ እንደክፍል ደረጃው ያብራሩላቸው በምሳሌም ደጋግመቀው ያስረዷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ቅጥያዎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ በምሳሌዎች ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ከተሰጣቸው ቃላት ውስጥ የመነሻ ቅጥያዎችን እንዲለዩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ቅጥያዎችን ከቃላት በመነጣጠል እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ሀ. ለመነሻ ቅጥያዎች ምልሶች፡፡

1. ስለ - ተከለ
2. አስ - ቀረ
3. እየ - ፈጠረ
4. በ - ፍጥነት
5. ሲ - ሄድ
6. ከ - ሰጠ
7. እንደ - ዕጽዋት
8. ስለ - ቤተሰብ
9. ቢ - ቀር
10. አስ - መለሰ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ቅጥያዎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ በምሳሌዎች ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ከተሰጣቸው ቃላት ውስጥ የመድረሻ ቅጥያዎችን እንዲለዩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ቅጥያዎችን ከቃላት በመነጣጠል እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ለ. ለመድረሻ ቅጥያዎች መልሶች፡፡

1. ተማሪ - ዎች
2. ልብስ - ህ
3. በሬ - ዎች
4. መምህር - ኦች
5. መጽሀፍ - ኤ
6. ክፍል -ኣችን
7. ድመት - ኦች
8. እርሳስ - ሽ
9. ቤት - ኡ
10. ሥራ - ኣችሁ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ቅጥያዎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ በምሳሌዎች ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ከተሰጣቸው ቃላት ውስጥ የመድረሻ ቅጥያዎችን ዋና ቃል እና የመድረሻ ቅጥያዎችን እንዲለዩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ሐ. ባለቅጥያ ቃላትን መነጣጠል ፡፡

| | ባለቅጥያ ቃላት | የመነሻ ቅጥያ | ዋና ቃል | የመድረሻ ቅጥያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለልብሶች | ስለ - | ልብስ | - ኦች |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2 | ከተወች | ከ - | ተወ | - ች |
| 3 | በደብተሩ | በ - | ደብተር | - ኡ |
| 4 | የአገራችን | የ - | አገር | - ኣችን |
| 5 | እንደሰጠን | እንደ - | ሰጠ | - ን |
| 6 | አልመሰለም | አል - | መሰለ | - ም |

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ቅጥያዎች እና ስለ ዓረፍተ ነገሮች የተማሩትን እንዲያስታውሱ በምሳሌዎች ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ባለቅጥያ ቃላትን በመጠቀም ነጠላ ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ አያያዥ ቃላት እና ስለ ዓረፍተ ነገሮች የተማሩትን እንዲያስታውሱ በምሳሌዎች ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ሠ. በአንቀጽ ውስጥ ያሉትን አያያዥ ዝርዝር፡፡

ምክንያቱም ፣ ስለሆነም ፣ ነገር ግን ፣ ስለዚህ

## የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ

መምህር

ተማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የምዕራፉን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ መረዳታቸውን በተማሪዎች መጽሀፍ ላይ የተቀመጡትን የምዕራፉን ማጠቃለያ ጥያቄዎች እንዲሰሩ በማደረግ ያረጋግጡ፤ እንዲሁም ከምዕራፉ ይዘት ጋር የሚገናኙ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመስጠት የምዕራፉን ትምህርት ያጠቃሉ፡፡

በዚህ ምዕራፍ ስር አዳምጦ እና አንብቦ የመረዳትን፣ የመናገር እና የመጻፍ ክሂሎችን አዳብረዋል፡፡

- ✓ ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍቺ ሰጥተዋል፡፡
- ✓ ስለ ቅጥያዎች ምንነት ገልጸዋል፤ የመነሻና እና የመድረሻ ቅጥያዎች ከቃላት ላይ መለየት ችለዋል፡፡
- ✓ ባለቅጥያ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን መስርተዋል፡፡
- ✓ አቀላጥፎ ለማንበብ የሚረዳቸውን ልምምድ በሚገባ አድርገዋል፤
- ✓ አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን መመስረት ችለዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት (፬)

## ሥርዓተ-ጾታ

**የተሰጠ ክፍለ ጊዜ 9**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ርዕሱን በመመልከትና በማዳመጥ ሃሳባቸውን ያካፍላሉ፤
- ካነበቡት ጽሁፍ ውስጥ ዝርዝር መረጃውን ይጽፋሉ፤
- ስለ አንቀጽ ምንነት ያብራራሉ፤
- የውሰት ቃላትን ጥቅም ይዘረዝራሉ፤

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ማዳመጥ እና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መጻፍ
- ሰዋሰው



### ማዳመጥ

### የሥራ ክፍፍል

**መምህር፡**

- **"የሥራ ክፍፍል"** የሚለውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡
- ምንባቡን በእርጋታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ቀድመው ምንባቡን ኮፒአድርጎ በመስጠት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ በሚገባ እያዳመጡ መሆናቸውን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያረጋግጡ፤
- ተማሪዎች የተዘጋጀውን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፤

## የሥራ ክፍፍል

በአርባ ምንጭ ከተማ የሚኖሩ እህትና ወንድም ነበሩ፡፡ ሁለቱም የሥርዓተ-ፆታ ክበብ አባላት ናቸው፡፡ ወንድምዬው በሥራ ክፍፍል አያምንም፤ ሥራም አይወድም፤ የቤቱን ሥራ ሁሉ የምትሰራው እህቱ ናት፡፡ በክበቡም ብዙ ተሳትፎ የለውም፡፡ እህትየው ግን ብዙ ስለምትሳተፍ ከክበቡ በርካታ ቁምነገር ተምራለች፡፡

ሀ. ከእህዬውና ከወንድምዬው በትምህርት ቤታቸው የስርዓተ ፆታ ክበብ ውስጥ የበለጠ የሚሳተፈው ማን ነው?

ለ. ከዚህ በመቀጠል ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?

ሆኖም በቤት ውስጥ ባለባት የሥራ ጫና ምክንያት የትምህርት ውጤቷ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጣ፡፡ በዚህም በጣም ተቆጨች፡፡ መብቷን በማስከበር ውጤቷን ለማሻሻል ወሰነች፡፡ ቤተሰቦቿ ባሉበት ጮክ ብላ፣ "ለመሆኑ ምግብ ማብሰልና ሕፃናትን መንከባከብ ለሴቶች፣ የሀብት ባለቤትነትን የመወሰን ስልጣን ለወንዶች ብቻ የሰጠ ማን ነው?" አለች፡፡ ወንድሟ "አያቶችሽ ይሆናሏ!" አላት፡፡ እሷም፣ "ያለንበት ዘመን ይህን አስተሳሰብ አይፈቅድም፤ ይህ አስተሳሰብ በማንኛችንም ቤት ውስጥ ሊኖር አይገባም" አለችው፡፡

አባትዬው "ዛሬ ምን አዲስ ነገር መጣ ልጄ?" አሏት፡፡ እሷም "ለውጤቴ መቀነስ ምክንያቱ ገብቶኛል፡፡" አለች፡፡ አባትዬውም ቶሎ ተረዷት፡፡ "ልጄ ሁሉንም ነገር አውቃለሁ! ከወንድምሽ ጋር ርስ በርሳችሁ ትተጋገዛላችሁ ብዬ ነው፤ የቤት ውስጥ ሥራውንም እኩል ተከፋፍላችሁ የምትሰሩ መስሎኝ ነው፡፡" አሏት፡፡

"አባዬ ወንድሜኮ የሚያጠፋው እያወቀ ነው፤ የሥርዓተ-ፆታ ክበብ ተጠሪያችን 'በወንድና በሴት መካከል ሥነ-ሕይወታዊ እንጅ ሌላ ልዩነት የለም፡፡' ብላለች፡፡ በመሆኑም፣ በቤታችን ውስጥ ልዩነት ሳይፈጠር፣ ላንዱ ባለማዳላት፣ በማህበራዊ ኑሯችን እኩል እንድንሆን ሊደረግ ይገባል፤ የድሮው አመለካከት እዚህ ላይ መቆም አለበት!" አለች ምርር ብላ፡፡ አባቷም፣ ወንድሟም፣ እናቷም ትክክለኛነቷን ተረዷት፡፡ አባቷም፣ "በይ ልጄ ከዛሬ ጀምሮ ሁላችንም የቤት ውስጥ ሥራችንን እኩል ተከፋፍለን እንሰራለን፡፡" አሏት፡፡ በቤተሰቡ አዲስና የተሳካ የሥራ ክፍፍል መስመር ተዘረጋ፡፡ እሷም በትምህርቷ ጥሩ ውጤት እያስመዘገበች በሕግ ትምህርት በዲግሪ ለመመረቅ በቃች፡፡

(ምንጭ፡-ከቀድሞው የ4ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የተወሰደ)

ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ የሚያውቁትን እንዲመልሱ ይጠይቋቸው/ያበረታቷቸው፡፡
- የተሰጠውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያድርጉ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓረፍተ ነገር የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ምሳሌዎችን በመስጠት ያስረዷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ለ. ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መልሶች፡፡

1. ያነሰ
2. በሩቅ
3. ያዘ
4. ጭካኔ
5. በተናጠል

## ጽህፈት

**መምህር፡**

❖ ተማሪዎች የሚያውቋቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲዘረዝሩ ያድርጉ፡፡

ምሳሌ፡-
- ቴሊቪዥን
- ሬዲዮ
- ማግኔት
- ሽሚዝ

❖ ስለውሰት ቃላት ምንነት እና ጥቅም የተዘጋጀውን ማስታወሻ ይጻፉላቸው፡፡

❖ በክፍል ደረጃቸው ልክ ስለውሰት ቃላት ምንነት እና ጥቅም ያብራሩላቸው፡፡

**መምህር፡**

### የውሰት ቃላት ምንነት

❖ የውሰት ቃል ማለት የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር በሚኖረው ግንኙነት (ኢኮኖሚያዊ፣ መልክዓምድራዊ፣ ማህበራዊ...) የተነሳ በሚፈጠር የእርስ በእርስ ንክኪ የሚመጣ ነው፡፡

**ለምሳሌ፡-**

ጳጳስ፣ ዲያቆን፣ ብርሌ፣ . . . የመሳሰሉትን ቃላት አማርኛ ቋንቋ ከግሪክ ቋንቋ የተዋሳቸው ቃላት ናቸው፡፡

❖ አማርኛ ቋንቋ ከሌሎች የአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ቋንቋዎች የተዋሳቸው በርካታ ቃላት አሉ፡፡

**ለምሳሌ፡-** ሠንጋ፣ ሽጋ፣ አዱኛ፣ ራዕይ፣ ሠናይ .... አማርኛ ከሀገር ውስጥ የተዋሳቸው ቃላት ናቸው፡፡

## የውሰት ቃላት ጥቅም

- የውሰት ቃላት ጥቅም ከሚያውሰው ቋንቋ ውስጥ ያለ አገላለጽ እና ሃሳብን ወደ ሚዋሰው ቋንቋ ውስጥ በቀጥታ በማስተላለፍ ሃሳቦች በማያሻማ አገላለጽ እንዲቀርቡ ማድረግ ነው፡፡

**ለምሳሌ፡-**

ሀ. **ኮምፒውተር** (የእንግሊዝኛ ቃል ነው፡፡) ይህን የቴክኖሎጂ ቃል አማርኛ በቀጥታ በመውሰድ እና በቋንቋው ቃል ውስጥ በማካተት እንዳለ እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡ ስለዚህ ይህ የቴክኖሎጂ ውጤት የያዘውን ሃሳብ የሚገልጽበት ሌላ ቃል ሳይፈልግ እንዳለ ሊጠቀምበት /ሊገልጽበት ችሏል ማለት ነው፡፡

ለ. **በርጩማ** (የኦሮምኛ ቃል ነው፡፡) ይህን ቃል አማርኛ ቋንቋ እንዳለ በመውሰድ ባለ ሶስት እግር መቀመጫ ለሆነው ቁስ መጠሪያ በማድረግ ተጠቅሞበታል፡፡ ስለዚህ በሌላ ቋንቋ ውስጥ ያለውን ሃሳብ በራስ ቋንቋ ሃሳብ ውስጥ በማካተተት እንድንገለገልበት በማድረግ የውሰት ቃላት ጥቅም አላቸው ማለት ነው፡፡

- ቀደም ብለው ተማሪዎች የአማርኛ የውሰት ቃላትን ከተለያዩ አማራጮች እንዲሰበስቡ ያድርጉ፤

| ተ.ቁ | በውሰት ወደአማርኛ የገባ ቃል | ቃሉ የሚገኝበት ቋንቋ (አዋሽ ቋንቋ) |
|---|---|---|
| 1 | እንሰት | ጉራግኛ |
| 2 | ፒንሳ | ጣሊያንኛ |
| 3 | በርጩማ | ኦሮምኛ |
| 4 | ኮምፒውተር | እንግሊዝኛ |
| 5 | ሻይ | አረብኛ |

መምህር፡-

❖ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ በአገር ውስጥ ከሚነገሩ የተለያዩ ቋንቋዎች እንዲሁም ከሀገር ውጪ ከሚነገሩ የተለያዩ ቋንቋዎች የተዋሳቸውን እና ቀጥታ በቋንቋው ውስጥ እየተጠቀመባቸው ያሉ ቃላትን ከመጽሀፍት በመፈለግ እና ሰዎችን በመጠየቅ ሰብስበው በማስታወሻ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ በሚከተለው መንገድ የተወሰኑ ምሳሌዎችንም ይስጧቸው፡፡ (ለመምህሩ ብቻ እንደ መነሻ እንዲሁነው የቀረበ)

| .ቁ | በውሰት ወደአማርኛ የገባ ቃል | ቃሉ የሚገኝበት ቋንቋ (አዋሽ ቋንቋ) |
|---|---|---|
| 1 | ቆጮ | ጉራ□ኛ |
| 2 | ሞባይል | እንግሊዝኛ |
| | አምባሻ | ትግርኛ |
| 3 | ሰንጋ | ኦሮምኛ |
| 4 | ሱቅ | አረብኛ |
| 5 | ጉዲፈቻ | ኦሮምኛ |
| 6 | ሰዓት | አረብኛ |
| 7 | ቢሮ | ፈረንሳይኛ |
| 8 | ባቡር | ፈረንሳይኛ |
| 9 | ፖስታ | ጣሊያንኛ |
| 10 | አባወራ | ኦሮምኛ |
| 11 | መርካቶ | ጣሊያንኛ |

❖ ተማሪዎች የውሰት ቃላት ናቸው ብለው የሚያመጧቸው ቃላት በትክክል ቃሉ የመጣበትን ቋንቋ በሚገባ እንዲጠቁሙ ያድርጉ፡፡

❖ በክፍል ውስጥ ዓይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃ እንደያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

❖ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም ቀድመው የውሰት ቃላትን ይሰብስቡ፡፡

ንባብ

## የጾታ እኩልነት

**መምህር፡**

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ "**የጾታ እኩልነት**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ጭውውት ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት ቀደምት ዕውቀታቸውን በመጠቀም የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- "**የጾታ እኩልነት**" በሚል ርዕስ በቀረበው ጭውውት ውስጥ ያለውን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡
- አራት ተማሪዎችን በመምረጥ እና በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ገጸባህርያት እንዲወክሉ በማድረግ ከተማሪዎቸ ፊት ሆነው የተሰጣቸውን ገጸባህሪ ንግግር እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- በተመሳሳይ ሌሎች ተማሪዎችንም በቡድን በማድረግ ገጸባህርያቱን በመወከል እንዲያነቡ ያበራታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜም ትክክለኛነትን ተከትለው እያነበቡ ስለመሆናቸው ይከታተሏቸው/ ይደግፏቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) "**የጾታ እኩልነት**" የሚለውን ጭውውት እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- (የሚቻል ከሆነ) ተማሪዎችን በመምረጥ እና ጭውውቱን ቀድመው እንዲያጠኑት በማድረግ በክፍል ውስጥ በድራማ መልክ እንዲያቀርቡት ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው መልሶቻቸውንም ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያብራሩ ያድርጉ፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ ምንባቡን እርስዎ ያንብቡላቸው፡፡ መልሶቻቸውንም ይቀበሏቸው፡፡

## ጽህፈት



**መምህር፡**

- ተማሪዎች ጭውውቱን መሰረት በማድረግ የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች በጽሁፍ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል ምላሻቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ቃላት አውዳዊ ፍቺ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡

(ማስታወስ የሚችሉባቸውን የተለያዩ ዘዴዎችን ተግባራዊ ያድርጉ)

- ለተሰጧቸው ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቻቸውን እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል ምላሻቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ክርክር ምንነት የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- የክፍሉን ተማሪዎች በተቀመጡበት በሁለት ምድብ ይመድቡና፤ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦችን በማንሳት እና ለሁለቱም ምድብ አንድ፤ አንድ ሃሳብ በመስጠት ይጠይቋቸው፡

ምሳሌ፡- ዕውቀት ወይስ ገንዘብ ይበልጣል (በሚሉ ሃሳቦች ላይ ሃሳብ እንዲያንሸራሽሩ ያድርጓቸው)

- ሃሳብ በሚያንሸራሽሩበትም ወቅት እርስዎ ለሁለቱም ምድብ ጥያቄዎችን ተራበተራ እየጠየቁ ያከራክሯቸው፤

ምሳሌ፡- የዕውቀት ቡድንን በመደገፍ

- ገንዘብን ማተም የሚቻለው ዕውቀት ሲኖር ነው፤ ስለዚህ ዕውቀት ከሌለ
- አንድ ሰው ዕውቀት ቢኖረውም ምግብ ለመግዛት ገንዘብ እንጂ ዕውቀት አያስፈልገውም፤ ስለዚህ ከዕውቀት ገገንዘብ ይበልጣል፡፡ በማለት እንዲከራከሩ ሁለቱንም ተራ በተራ ያግዟቸው፡፡

- (በተጨማሪ) ሌሎች ርዕሶችን እያነሱ እንዲከራከሩ ያበረታቷቸው፡፡

ገንዘብ ማተም አይቻልም፡፡ የሚል ሃሳብ ያንሱ፤

በመቀጠል፡- የገንዘብ ቡድንን በመደገፍ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች በሚከራከሩበት ወቅት እርስዎ ተማሪዎቹ ተራ እየጠበቁ በስርዓት ሃሳባቸውን እንዲያስረዱ ያድርጉ፤
- ተማሪዎች በዚህ መልክ ለተወሰኑ ደቂቃዎች እንዲከራከሩ ካደረጉ በኋላ ስለ ክርክር ምንነት ከአውዱ የተረዱትን እንድናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ስለ ክርክር ምንነት እና መመሪያ አጭር ማስታወሻ ይጻፉላቸው፡፡
- ተማሪዎችም ማስታወሻውን በሚገባ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

## ክርክር

- ክርክር ማለት፡- ሁለት ሰዎች ወይም ቡድኖች ዳኛ በመሰየም የሚያደርጉት ስርዓታዊ ሙግት (የሃሳብ ልውውጥ) ነው፡፡ ክርክር ከጭውውት የሚለየው በመጨረሻ አሸናፊ እና ተሸናፊ ያለበት እንዲሁም ዳኛ የሚሰየምበት በመሆኑ ነው፡፡
- ክርክር ለማድረግ ስንዘጋጅም ሆነ ስንከራከር የሚከተሉትን መመሪያዎች ማስታወስ ይገባል፡፡

**የክርክር ቅድመ ዝግጅት ጊዜ**

√ ስለምንከራከርበት ርዕሰ ጉዳይ መረጃ መሰብሰብ (ከሰዋች፣ከመጽሀፍት...)

√ የተሰበሰበውን መረጃ በቅደም ተከተል መያዝ

√ ልምምድ ማድረግ

**ክርክር በሚደረግበት ጊዜ** √ የመከራከሪያ ርዕስን ለአድማጭ ማስተዋወቅ

√ ያልተፈለገ የአካል እንቅስቃሴ አለማድረግ

√ ለክርክሩ የተሰጠውን የጊዜ ገደብ ማክበር

√ ከርዕሱ ወጭ የሆነ ሐሳብ አለማቅረብ

√ አድማጭን ማመስገንና የዳኞቹን ውሳኔ መቀበል . . . ናቸው፡፡

- ❖ የተዘጋጀውን ማስታወሻ በክፍል ደረጃቸው ልክ ያብራሩላቸው፡፡
- ❖ ለቀጣይ ክፍለ ጊዜ በቤት ውስጥ የወንዶች እና የሴቶች ሚና ምን መሆን አለበት? በሚል ርዕስ ለክርክር እንዲዘጋጁ ያድርጉ፡፡

**መምህር፡**

- ➢ ተማሪዎች ስለ ክርክር ምንነት እና መመሪያ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠል በቡድን በማድረግ የተዘጋጁበትን ክርክር በመመሪያው መሰረት እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡ ከመካከላቸውም ዳኛ፣ ተከራካሪዎች እና በመመሪያ መሰረት ነጥብ የሚይዙ ተማሪዎችን በመመደብ ክርክርን በተግባር እንዲከራከሩ ያድርጉ፡፡

## መናገር

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ አንቀጽ ምንነት የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች መጽሐፎቻቸውን እንዲያወጡ በማድረግ ከመጽሐፎቻቸው ውስጥ አንድ ምንባብ በመምረጥ እና ያንን ምንባብ ሁሉም ተማሪዎች እንዲመለከቱት በማድረግ የሚመለከቱት ምንባብ የተጻፈበትን ቅርጽ በመውሰድ አንቀጽ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይግለጹላቸው፡፡
- ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ከገለጻው የተረዱትን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡

### የአንቀፅ ምንነት እና ቅርጽ

- **አንቀፅ ማለት** ከአንድ በላይ የሆኑ እና አንድ ሃሳብ የሚገልጹ ዓረፍተነገሮች ያሉት ፅሁፍ ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ አንቀፅ ውስጥ ያሉ ዓረፍተነገሮች የሃሳብ **አንድነት** ያላቸው፣ **የሚደጋገፉና የተያያዙ** ሊሆኑ ይገባል፡፡

- በአንድ አንቀፅ ውስጥ የሚኖረው ሀሳብ አንድ ብቻ ነው፡፡

**የአንቀፅ አጻጻፍ ቅርጽ**

1ኛ ከግራ ወደቀኝ ገባ ብሎ መጻፍ

2ኛ በአንቀጾች መሃል አንድ መስመር በመተው መጻፍ

- አንድ አንቀፅ ሲፃፍ ዓረፍተነገሮቹ በሚገባ ቅደምተከተላቸውን ጠብቀው መደርደር አለባቸው፡፡

ለምሳሌ፡- የሚከተሉትን ተዘበራርቀው የተቀመጡ ዓረፍተነገሮች ቅደም ተከተላቸውን በማስተካከል አንድ አንቀፅ መመስረት ይቻላል፡፡

ሀ. ቡና ለእንግዳ ተፈላ፡፡
ለ.ሉፓኪ ቡና ገዝቶ መጣ፡፡
ሐ. እንግዳው ወደቤቱ ሄደ፡፡
መ.ሉፓኪ ቡና እንዲገዛ ሱቅ ተላከ፡፡
ሠ. እነሉፓኪ ቤት እንግዳ መጣ፡፡

**መምህር፡**

- የትኛውንም የአንቀጽ ቅርጽ ተከትለን ስንጽፍ የሃሳብ ልዩነት እንደማያመጣ እና በአንድ ጊዜ ሁለቱን የአንቀጽ ቅርጾች በመደባለቅ መጻፍ እንደማይቻል ያስረዷቸው፡፡
- የተዘጋጀውን ማስታወሻ በክፍል ደረጃቸው ልክ ያብራሩላቸው፡፡
- በተለይ ባለንበት ወቅት የሁለተኛውን የአንቀጽ አጻጻፍ ቅርጽ ተከትሎ እንደሚጻፍ ይግለጹላቸው፡፡

## ጽህፈት

እነ ሉፓኪ ቤት እንግዳ ስለመጣ ሉፓኪ ቡና እንዲገዛ ሱቅ ተላከ፡፡ ሉፓኪ ቡና ገዝቶ ከመጣ በኋላ ቡናው ለእንግዳው ተፈላ፡፡ እንግዳውም ቡናውን ጠጥቶ ወደቤቱ ሄደ፡፡

እነ ሉፓኪ ቤት እንግዳ ስለመጣ እና ሉፓኪ ቡና እንዲገዛ ሱቅ ተላከ፡፡ ሉፓኪ ቡና ገዝቶ ከመጣ በኋላ ቡናው ለእንግዳው ተፈላ፡፡ እንግዳውም ቡናውን ጠጥቶ ወደቤቱ ሄደ፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ አንቀጽ ምንነት እና ቅርጽ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን ይጠቀይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተዘበራርቀው የተሰጧዋቸውን ዓረፍተነገሮች በማስተካከል በአንቀጽ ቅርጽ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ ቅደም ተከተሉን በማስተካከል በቃል እዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

**የተዘበራረቁ ዓረፍተነገሮችን ቅደም ተከተል በማስተካከል እና ቃላቱን በማስማማት የተጻፈው አንቀጽ መልስ፡፡ (ለምሳሌ)**

ዮሴፍ ቆሻሻ ሸቶት ራሱን ስላመመው እናቱ በጣም ተጨነቁ፡፡ ከዛም ዳማከሴ ቆርጠው በመዳፋቸው በማሸት ትንሽ እንዲቆይ ካደረጉ በኂላ በግማሽ ማንኪያ አድርገው አጠጡት፡፡ የእራስ ምታቱም ቀነሰለት፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለአንቀጽ ምንነት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች የተሰጣቸውን ቃላት በመጠቀም እና የቀለሙን ቅደም ተከተል በመጠበቅ አንድ አንቀጽ እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡

**ለ. የቀለም ቅደም ተከተልን በመከተል የተመሰረተ አንቀጽ መልስ፡፡**

ሴቶች ለአገር ባለውለታዎች ናቸው፡፡ አስተሳሰባቸውም ብሩህ ነው፡፡ ብልሃትና ጥበብም አላቸው፡፡ የማገናዘብ ችሎታቸውም ከፍተኛ ነው፡፡ ከችኩልነት ይልቅ መረጋጋትን ይመርጣሉ፡፡ ጥንካሬያቸውም በማህበረሰቡ ዘንድ ይታወቃል፡፡ ለዚህም "ሴት ልጅ ብልህ ናት፡፡" የሚለውን አባባል ማንሳት ይቻላል፡፡

## ሰዋስው

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ወይንም ሃሳባቸውን በዓረፍተ ነገር እንዲገልጹ የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡ በሚናገሩት ሃሳብ ውስጥ ሃሳባቸውን የቋጨበት ቃል ግስ መሆኑን ይግለጹላቸው፡፡
- ተማሪዎች ስለ ግስ ምንነት የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ስለ ግስ የተዘጋጀውን ማስታወሻ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

### ግስ

**ግስ ማለት** ፡-የዓረፍተነገር ማሰሪያ/መቋጫ / መደምደሚያ/ በመሆን የሚያገለግል ቃል ነው፡፡ ግስ በሚባለው የቃል ክፍል ውስጥ የሚመደቡ

ምሳሌ፡- ጻፈ፣ ተማረ፣ አነበበ፣ ተጫወተ፣ ነው፣ አለ. . .

- ማስታወሻውን በክፍል ደረጃቸው ልክ በምሳሌ ያብራሩላቸው፡፡
- ጥያቄዎችንም እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

ቃላት "ድርጊትን" ወይም "ሁነትን" ያመለክታሉ፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ከራሳቸው ስም በመጀመር በክፍል ውስጥ ያሉትን ቁሳቁሶች፣ ራሳቸው የሚይዟቸው የመማሪያ ቁሳቁሶቻቸውን ሁሉ ተራ በተራ እንዲጠሩ ያድርጉ፤ ያበረታቷቸው፡፡ የሚጠሩት ቃል ስም መሆኑን ይግለጹላቸው፡፡
- ተማሪዎች ስለ ስም ምንነት የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ስለ ስም የተዘጋጀውን ማስታወሻ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

## ስም

**ስም ማለት** የቦታ፣ የሰው፣ የቁሳቁስ፣ የእንስሳት፣ የዕፅዋት. . . መጠሪያ ሲሆን -ኦች ወይም -ዎች የሚል አብዣ ቅጥያዎችን የሚወስድ ቃል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዓረፍተነገር ውስጥ ባለቤት (ድርጊት ፈጻሚ) በመሆን ያገለግላል፡፡

- ማስታወሻውን በክፍል ደረጃቸው ልክ በምሳሌ ያብራሩላቸው፡፡
  ምሳሌ፡- *መምህሩ ጽሁፍ ጻፈ፡፡* (መምህር ስም ነው፤ የመጻፍ ድርጊት የፈጸመው መምህሩ ነው ስለዚህ የዓረፍተነገሩ ባለቤት መምህሩ ነው)
- ጥያቄዎችንም እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለስም፣ ስለግስ እና ስለዓረፍተ ነገር የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፤
- ተማሪዎች ስሞችን ወደ ግስ በመቀየር እንዲጽፉ ምሳሌዎችን በመስጠት ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ዓይነ ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ

**መምህር**

ተማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የምዕራፉን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ መረዳታቸውን በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተቀመጡትን የምዕራፉን ማጠቃለያ ጥያቄዎች እንዲሰሩ በማድረግ ያረጋግጡ፤ እንዲሁም ከምዕራፉ ይዘት ጋር የሚገናኙ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመስጠት የምዕራፉን ትምህርት ያጠቃሉ።

- ✓ በዚህ ምዕራፍ ስር አዳምጦ እና አንብቦ የመረዳትን፣ የመናገር እና የመጻፍ ክሂሎችን አዳብረዋል።
- ✓ ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍች ሰጥተዋል።
- ✓ የውሰት ቃላት ምንነትን እና ጠቀሜታ ለይተዋል።
- ✓ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ የውሰት ቃላትን ለመለየት ጥረዋል፤ በክፍል ውስጥም ሰብስበው በማምጣት አቅርበዋል።
- ✓ የክርክር ምንነትን እና መመሪያዎችን አውቀዋል፤ ክርክርም ማድረግ ችለዋል።
- ✓ የአንቀጽ ምንነትን አውቀዋል። ዓረፍተነገሮችን በማቀናጀት አንቀጽ መመስረት እና መጻፍ ችለዋል።

# ምዕራፍ   አምስት (፭)

## ጉብኝት

**የተሰጠ ክፍለ ጊዜ 9**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ስለጉብኝት መዳረሻዎች ያዳመጡትን በቃላቸው ዘገባ ያቀርባሉ፡፡
- ምንባብ አንብበው የተረዱትን ይገላጻሉ፡፡
- የአንቀጽ ባህሪያትን ይለያሉ፡፡
- አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም አረፍተነገር ይመሰርታሉ፡፡
- ገላጮችን በመጠቀም አረፍተነገር ይመሰርታሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ማዳመጥ እና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መጻፍ
- ሰዋሰው



### ማዳመጥ

## በደቡብ ክልል የሚገኙ የቱሪስት መስህቦች

**መምህር፡**

- **"የደቡብ ክልል መስህቦች"** የሚለውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡
- ምንባቡን በእርጋታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ቀድመው ምንባቡን ኮፒ አድርገው በመስጠት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ በሚገባ እያዳመጡ መሆናቸውን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያረጋግጡ፤
    - ተማሪዎች የተዘጋጀውን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፤

## የደቡብ ክልል መስህቦች

በደቡብ ክልል በርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መስህቦች ይገኛሉ፡፡ ተፈጥሯዊ ከሆኑት መካከል ሀይቆች፣ በፓርኮች ውስጥ የሚገኙ የዱር እንስሳት፣ ፏፏቴዎችና የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከሃይቆች መካከል የአባያ፣ የጫሞና የአረቅጥ ሃይቆች ይጠቀሳሉ፡፡ የነጭ ሳር፣ የማጎ፣ የጊቤ ሸለቆና የማዜ ብሔራዊ ፓርኮች ከተፈጥሯዊው መስህቦች መካከል ናቸው፡፡ ከፏፏቴዎች መካከል በወላይታና በከምባታ ጠምባሮ ዞኖች ድንበር የሚገኘው የአጆራ ፏፏቴ፣ በየም ልዩ ወረዳ የሚገኘው የብርብርሳ ፏፏቴና በጉራጌ ዞን ፣ በአዣ ወረዳ የትራር እንዲሁም በእነሞርና በቸሃ ድንበር ያለው ቃሽቃሽየ ፏፏቴ ይጠቀሳሉ፡፡ ከነዚህም ሌላ የኮንሶው "ኒውዮርክ" መልክዐ ምድርና በኣርባ ምንጭ በሁለቱ ሃይቆች መካከል የሚገኘው የእግዜር ድልድይ ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የኮንሶ ባህላዊ የእርከን አሰራር በመቃብር ላይ የሚደረግ የዋካ ሐውልት፣ የጌዲኦ ቱቲቲና ቱቱፈላ ትክል ድንጋዮች፣ እንዲሁም በጉራጌ ዞን የሚገኘው የጢያ ትክል ድንጋይ ሰው ሰራሽ የቱሪስት መስህቦች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የብሔር ብሔረሰቦች አልባሳትና መገልገያ እቃዎች ይጠቀሳሉ፡፡

በጋሞ ጎፋ ዞን በአርባምንጭ ከተማ በስተምሥራቅ በሚገኘው ነጭሳር ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ የሜዳ አህያ፣ የሜዳ ፍየል፣ ከርከሮ የመሳሰሉት እንስሳትና በርካታ የአዕዋፍ ዝርያዎች ይገኛሉ፡፡ በደቡብ ኦሞ ዞን የማጎ ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ ቀጭኔ፣ ዝሆንና የመሳሰሉት ሲገኙ፣ በጉራጌ ዞን በጊቤ ሸለቆ ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ አንበሳና ነብርን ጨምሮ አሥራ ስድስት አይነት ትላልቅ አጥቢ እንስሳት ይገኛሉ፡፡

ከነዚህ ሌላ በካፋ ዞን የሚገኘው የማኪራ ጥብቅ ደንና የጫካ ቡና እንዲሁም እናት ቡና እየተባለ የሚጠራው የቡና ዛፍ ለአካባቢው ገጽታ አስደሳች መስህብ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች በደቡብ ክልል የሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መስሕቦች ናቸው፡፡ አነዚህንም ለመጎብኘት ብዙ የውጪና የሀግር ውስጥ ጎብኚዎች በየእለቱ የሚጎበኟቸው ቦታዎች ናቸው፡፡

(ምንጭ በ2009 ዓ.ም ከታተመው የአራተኛ ክፍል የተማሪው መጽሐፍ የተወሰደ)

## ቃላት

**መምህር፡**

- **"የደቡብ መስህቦች"** በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በተመጠነ የድምጽ ደረጃ እና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ስለቃላት አውዳዊ ፍቺ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ይጠይቋቸው/ያበረታቷቸው፡፡
- የተሰጠውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያድርጉ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

- "አለ" ወይም ሌላ ተመሳሳይ ቃል (በማጥበቅ እና በማላላት ሲነበብ የተለያየ ትርጉም የሚሰጥ ቃል) በመስጠት ተማሪዎች ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡

ምሳሌ ተማሪዎች፡- 1. አባቴ ቤት ውስጥ አለ፡፡

2. አባቴ እመጣለሁ አለ፡፡ . . . "ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡ "በዚህም መሰረት ቃሉን ሲጠቀሙ አጥብቀው ወይም አላልተው ስለመሆኑ በመሰረቱት ዓረፍተነገር ውስጥ ቃሉ የያዘውን ትርጉም በመግለጽ ያብራሩላቸው፡፡

| ቃል | ሲጠብቅ የሚኖረው ትርጉም | ሲላላ የሚኖረው ትርጉም |
|---|---|---|
| አለ | ይገኛል | ተናገረ |

- በተመሳሳይ ሌሎች በማጥበቅ እና በማላላት ሲነበቡ የተለያዩ ትርጉሞችን የሚሰጡ ቃላትን በመስጠት ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡

## ሐ. በዓረፍተ ነገር ውስጥ ጠብቀው እና ላልተው  የገቡ ቃላት መልሶች፡፡

1. ጠብቆ ፤ ላልቶ
2. ጠብቆ ፤ ላልቶ
3. ላልቶ ፤ ጠብቆ
4. ላልቶ ፤ ጠብቆ
5. ላልቶ ፤ጠብቆ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓረፍተነገር ምንነት የተማሩትን በተመለከተ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ቃላት በመጥበቅ እና በመላላት ሲነበቡ የተለያየ ትርጉም መስጠት እንደሚችሉ ቀድመው የተማሯቸውን ጥያቄዎች በማንሳት ክለሳ ያድርጉላቸው፤
- ቃላት በመጥበቅ እና በመላላት ሲነበቡ የሚሰጡትን ትርጉም የሚያሳይ ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ ያግዟቸው፡፡



### ጽህፈት

## መ. ቃላት በማጥበቅ እና በማላላት ስናነባቸው የሚሰጡትን የተለያየ ትርጉም የሚያሳይ መልሶች፡፡

1. ቀናት    ተሳካላት (ጠብቆ)

   ዕለታት (ሲላላ)

2. አያት    ተመለከታት (ሲጠብቅ)

   የእናት ወይም የአባት እናትና አባት (ሲላላ)

3. ለጋ    ጠለዘ/መታ (ሲጠብቅ)

   ያልበሰለ (ሲላላ)

4. ያነባል    የተጻፈውን ነገር ይረዳል (ሲጠብቅ)

   ያለቅሳል (ሲላላ)

5. ጥልቅ    ዘው ማለት(ሲጠብቅ)


   ሩቅ (ሲላላ)

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓረፍተ ነገር ምንነት የተማሩትን በተመለከተ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው።
- የተሰጡትን አዳዲስ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድጉ፤ እርማትም ይስጧቸው።
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው።

**መምህር፡**

- "የደቡብ ክልል መስህቦች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በተመጠነ የድምጽ ደረጃ እና በተገቢው ፍጥነት ያንብቡላቸው።
- መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በቅድሚያ ምንባቡን ኮፒ በማድረግ ይስጧቸው።
- ያዳመጡትን ምንባብ ሃሳብ በአራት አረፍተነገሮች እንዲጽፉ ያበረታቷቸው።



## ንባብ

## አዲስ አበባ እና ቤተ-መዘክሮቿ (ሙዚየሞቿ)

**መምህር፡**

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ "**አዲስ አበባ እና ቤተ-መዘክሮቿ (ሙዚየሞቿ)**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት ቀደምት ዕውቀታቸውን በመጠቀም የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው።

- ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- **"አዲስ አበባ እና ቤተ-መዘክሮቿ (ሙዚየሞቿ)"** በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ለእነዚህ ተማሪዎች ለብቻቸው እርስዎ ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ለድህረ ንባብ የቀረቡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) **"አዲስ አበባ እና ቤተ-መዘክሮቿ (ሙዚየሞቿ)"** የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ለብቻቸው ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ስለተመሳሳይ ቃላት የተማሩትን በተለያዩ ስልቶች እንዲያስታውሱ ያድርጉ፤
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

ሀ. ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መልሶች፡፡

1. ጥንታዊ
2. ስዕል/ገጽታ
3. ታሪክ/ጀብድ
4. መጣበቅ/ማጣበቅ
5. ከለላ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) **"አዲስ አበባ እና ቤተ-መዘክሮቿ (ሙዚየሞቿ)"** የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ለብቻቸው ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡

- ተማሪዎች ስለተቃራኒ ቃላት የተማሩትን በተለያዩ ስልቶች እንዲያስታውሱ ያድርጉ፤

- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡ ፡

**ለ.** ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተቃራኒ ፍቺ መልሶች፡፡

1. የማይስብ
2. አፈረሰ
3. ሰውሰራሽ
4. ራቀ
5. ኩረጃ

## ጽህፈት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች በጽህፈት ስር ተዘጋጁ ጥያቄዎችን በትዕዛዙ መሰረት እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፤
- ተማሪዎች ስለዓረፍተ ነገር ምንነት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን የተሟላ ሃሳብ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር:**

- ተማሪዎች ስለዓረፍተ ነገር ምንነት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው።
- ተማሪዎች የሚሰጧቸውን ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው። እንዲሁም በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው።

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር:**

- ተማሪዎች አቀላጥፎ የማንበብ ደረጃ ላይ ደረሱ የምንለው 1. **ትክክለኛነት** 2. **ፍጥነት** እና 3. **ድምጸት (ስርዓተ-ነጥቦችን በመከተል የጥያቄ፣ የማጋነን. . .)** ስልትን ተከትለው ድምጻቸውን እንደ ዓረፍተነገሩ ይዘት በመቀያየር ማንበብ ሲችሉ ነው። ስለሆነም ከዚህ ቀደም ባሉ ምዕራፎች ተማሪዎች ለአቀላጥፎ ንባብ የንባብ ትክለኛነትን እንዲለማመዱ ተደርጓል። **በዚህ ምዕራፍ ደግሞ** ተማሪዎች ቃላትን በሚገባ ወይም **ትክክለኛነትን** ተክትለው ከማንበብ በዘለለ ተገቢውን ፍጥነት በመጠበቅ እንዲያነቡ በማድረግ ንባብን እንዲያዳብሩ ያድርጓቸው።
- በተማሪ መጽሀፍ ላይ "**ደቡብ ክልል**" በሚል ርዕስ የቀረበውን አንቀጽ ተማሪዎች በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) በተናጠል በመደጋገም እንዲያነቡ ያድርጉ።
- የተለያዩ የንባብ ስልቶችን በመጠቀም በጥንድ፣ በጋራ. . . ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ እንዲለማመዱ ያድርጉ
- ተማሪዎች በሚሰጧቸው ደቂቃ ውስጥ ከጓደኞቻቸው ፊት በመሆን "**ደቡብ ክልል**" የሚለውን አንቀጽ ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድርጓቸው።
- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ተገቢውን **የንባብ ፍጥነት** ተከትለው ማንበባቸውን ይከታተሉ፤ ማስታወሻዎችንም በመያዝ በተገቢው የፍጥነት ደረጃ ያላነበቡ ተማሪዎችን የሚደግፉበት ስልት በመቀየስ የንባብ ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ ይደግፏቸው።
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ንባቡን እንዲያዳምጡ በማድረግ የምንባቡ ሃሳብ ስለምን እንደሆነ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው።

## ✍ጽህፈት

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎች ባለፉት ምዕራፎች ስለአንቀጽ ምንነት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በዚህ ምዕራፍ የአንቀጽ ባህሪያትን እንዲለዩ ያድርጓቸው፤
- ❖ ስለአንቀጽ ባህርያት የተዘጋጀውን ማስታወሻ ይጻፉላቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎችም ማስታወሻውን በሚገባ እንዲጽፉ ያድርጉ፤ ያብራሩላቸውም፡፡

### የአንቀፅ ባህርያት

አንቀፅ በውስጡ አንድ ነጠላ ሃሳብን የሚይዝ የድርሰት (የጽሁፍ ) አካል ነው፡፡ **(በተማሪዎች ደረጃ የአንድ ምንባብ አንድ አካል ነው በሚል ያስረዷቸው)** አንቀጽ ሦስት የተለያዩ ባህሪያት አሉት፡፡ እነሱም፡-

1. **አንድነት፡-** በአንቀጹ ውስጥ የሚገኙ ዓረፍተ ነገሮች ስለአንድ ጉዳይብቻ የሚያወሩ መሆን እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው፡፡
2. **ውህደት፡-** በአንቀጹ ውስጥ የሚገኙ ዓረፍተነገሮች የሚያስተላልፉት ሃሳብ እርስ በእርስ የተገናኘ ወይም የርስበርስ መተሳሰርን የሚያሳ ነው፡፡
3. **አፅንኦት፡-** በአንቀፁ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገው ሀሳብ ጎልቶ እንዲታይ የሚያደርግ ዓረፍተነገር መያዝን የሚያመለክት ነው፡፡

- ❖ ማስታወሻውን በክፍል ደረጃቸው ልክ ብቻ ያብራሩላቸው፡፡

ለምሳሌ፡- (እንደአማራጭ) ተማሪዎች ስለ ሻይ አጠቃላይ ሁኔታ እንዲያስቡ አንድ ደቂቃ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል በሚከተለው መንገድ የአንቀጽ ባህርያትን በሻይ አስተሳስረው ያስረዷቸው፡፡ ፡-

#### የአንቀጽ አንድነትን ለማስረዳት

- ✓ "አንድን ሻይ" ሻይ ብለን የምንጠራው ፤ የፈላው ውሃ፣ የሻይ ቅመም/ሻይ ቅጠል እና ስኳር በአንድነት ተዋህደው/ተቀላቅለው የሚፈጥሩት ሲሆን ነው፡፡ ለምሳሌ ሻይ ቅጠል የሌለውን "ሻይ" ሻይ ብለን አንጠራውም፡፡ ስለ አንድ ጉዳይ ብቻ **የማያወሩ** አረፍተነገሮች የተቀላቀሉበትንም "አንቀጽ" አንቀጽ አንለውም፡፡

#### የአንቀጽ ውህደትን ለማስረዳት

- ✓ የፈላ ሻይ ውስጥ ስኳር ጨምረን ካማሰልነው በኋላ ሻዩን ከስኳሩ መለየት አንችልም ምክንያቱም ስለተዋሃደ፤ አንቀጽም እንዲህ ነው በውስጡ ያሉ ዓረፍተነገሮች እርስ በእርስ ተዋህደው ከተጻፉ አንዱ ለአንዱ አስፈላጊ ስለሚሆን ያፈነገጠ ወይም ከዋናው ሃሳብ የወጣ ዓረፍተ ነገር አናገኝም፡፡

#### የአንቀጽ አጽንኦትን ለማስረዳት

- ✓ በሻይ ውስጥ፡- የፈላ ውሃ፣ የሻይ ቅመም/ሻይ ቅጠል እና ስኳር አለ፡፡ ነገር ግን ጎልቶ የሚታየን የፈላውን ውሃ ከለር የቀየረው የሻይ ቅጠሉ ቀለም ነው፡፡ በአንቀጽ ውስጥም ከሚገኙ ዓረፍተነገሮች እና አያያዥ ቃላት ውስጥ ጎልቶ የሚወጣው **ምን አነበብን?** ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ በአንቀጹ ውስጥ አጽንኦት/ትኩረት የተሰጠበት ዋና ሃሳብ ነው፡ .

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ አንቀጽ ባህርያት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ተዘበራርቀው የተደረደሩ ዓረፍተ ነገሮችን በማስተካከል አንቀጽ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

## ሀ. የዓረፍተነገሮች ቅደም ተከተል በማስተካከል አንቀጽ መጻፍ መልስ፡፡(በዚህ መልኩ ሊቀርብ ይችላል)

ዓይናለም የምልክት ቋንቋ ለመልመድ ስለምትፈልግ የምልክት ቋንቋ የምትችለው ጓደኛዋ እንድታስተምራት ጠየቀቻት፡፡ ጓደኛዋም ቀስ በቀስ የምልክት ቋንቋውን አለማምዳት ዓይናለም በአጭር ጊዜ የምልክት ቋንቋ መጠቀም ቻለች፡፡ በዚህም ደስተኛ ሆነች፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ አንቀጽ ባህርያት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በትምህርት ቀናቸው ትምህርትቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከገቡበት ሰዓት አንስቶ እስከ እረፍት ሰዓት ድረስ የሰሩትን ዋና ዋና ተግባር የአንቀጽ ባህርያትን በመጠበቅ በአንድ አንቀፅ ጽፈው ለክፍል ጓደኞቻቸሁ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡ (ይህን ተግባር ክፍለጊዜው ከመድረሱ በፊት ቀደም ብለው ባሉት ቀናት እንዲዘጋጁበት ያድርጉ፡፡)
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ሰዋስው

**መምህር፡**

- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶች ያላቸውን ከለር(ቀለም) መጠን፣ ብዛት፣ ቅርጽ፣ ወገን፣ እንዲሁም ሰዎች እና እንስሳት ያላቸውን ባህሪያት. . . እንዲናሩ ያበረታቷቸው/ተማሪዎች በሚመልሱበትም ወቅት በጥቁር/ነጭ ሰሌዳ ላይ መልሶቻቸውን በመጻፍ ያበረታቷቸው፡፡
- እንዲሁም ስለ አንድ ነገር የተለያ ገላጮችን በመጠቀም እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፤

ለምሳሌ፡- ጥቁር/ነጭ ሰሌዳውን በመመልከት የሰሌዳውን መጠን፣ ቅርጽ፣ ቀለም፣ ጥራት፣ . . . እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

- እነዚህ የሚጠሯቸው ነገሮች የስም ገላጭ ቃላት መሆናቸውን ይግለጹላቸው፡፡

**መምህር፡**

- ስለ ገላጭ ቃላት የተዘጋጀውን ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡
- ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

### ገላጭ ቃላት

ከስም በፊት ወይም ኋላ በመግባት ስለስሙ ቅርጽ፣ ቀለም፣ ብዛት፣ ባህሪ፣ ወገን. . . ምን እንደሚመስል የሚገልጽልን ሲሆን በስሙ ዙሪያ ከነበረን እውቀት ላይ ተጨማሪ መረጃ (ዕውቀት) እንዲኖረን የሚያደርግ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ወፍራም በግ　　　በጉ ትልቅ ነው፡፡

ሹራቡ ጥቁር ነው፡፡　　　ደግ ሰው

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለገላጭ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- የተዘጋጀውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**ሀ. በዝርዝር ለተቀመጡ ገላጭ ቃላት መልሶች፡፡**

1. ቀለም 2. ብዛት 3. ባህሪ
4. ወገን 5. ቅርጽ 6. መጠን

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለገላጭ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- የተዘጋጀውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያበረታቷዋቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**ሐ. በዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ገላጭ ቃላት መልሶች፡፡**

1. ቸር 2. በርካታ 3. ኢትዮጵያዊ
4. ትልቅ 5. ነጭ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለገላጭ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎችን በጥንድ ወይም በቡድን (4/6 ተማሪ ባልበለጠ) እንዲቀመጡ ያድርጉ፡፡
- ገላጭ ቃላትን በየዓይነታቸው (በየምድባቸው) እንዲያስቀምጡ አበረታቷቸው፤ ለመልሶቻቸውም እርማት ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለገላጭ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ገላጭ ቃላትን በዓፍተነገር ውስጥ በመጠቀም እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ**

***መምህር***

*ተማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የምዕራፉን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ መረዳታቸውን በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተቀመጡትን የምዕራፉን ማጠቃለያ ጥያቄዎች እንዲሰሩ በማድረግ ያረጋግጡ፤ እንዲሁም ከምዕራፉ ይዘት ጋር የሚገናኙ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመስጠት የምዕራፉን ትምህርት ያጠቃሉ፡፡*

- ✓ በዚህ ምዕራፍ ስር አዳምጦ እና አንብቦ የመረዳትን፣ የመናገር እና የጽህፈት ክሂሎችን አዳብረዋል፡፡
- ✓ ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍቺ ሰጥተዋል፡፡
- ✓ የአንቀጽ ባህርያትን ለይተው ተረድተዋል፡፡
- ✓ አቀላጥፎ ለማንበብ የሚያግዝ ልምምድ አድርገዋል፡፡
- ✓ አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን መስርተዋል፡፡
- ✓ የገላጭ ቃላትን ምንነት ተረድተዋል፡፡
- ✓ ገላጭ ቃላትን በየዓይነታቸው መመደብ ችለዋል፡፡
- ✓ ገላጭ ቃላትን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በመጠቀም አሳይተዋል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት (፮)

## ስፖርት

**የተሰጠ ክፍለ ጊዜ 9**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ያዳምጡና በቃላቸው ሃሳብ ይለዋወጣሉ፡፡
- እያንዳንዱን አንቀጽ አንብበው ከጽሁፉ ውስጥ ያገኙትን ሃሳብ ያብራራሉ፡፡
- የቃላት እውቀታቸውን ያሳድጋሉ፡፡
- ባለቤትና ግስን አስማምተው አረፍተነገር ያዋቅራሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ማዳመጥ እና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መጻፍ
- ሰዋስው



### ማዳመጥ

### የኦሎምፒክ ወርቆች

**መምህር፡**

- "የኦሎምፒክ ወርቆች" የሚለውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡
- ምንባቡን በእርጋታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ቀድመው ምንባቡን ኮፒ አድርገው በመስጠት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ በሚገባ እያዳመጡ መሆናቸውን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያረጋግጡ፤
- ተማሪዎች የተዘጋጀውን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፤

## የኦሎምፒክ ወርቆች

"ብራዚል የሌለችበት የዓለም ዋንጫ አይደምቅም፡፡" እንደሚባለው ሁሉ ኢትዮጵያ የሌለችበት የኦሎምፒክ ውድድር አንዳች እንደሚጎድለው ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ለዚህ ምስክር ቁጠሩ ብንባል በተለያየ ጊዜ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በኦሎምፒክ መድረክ የፈጸሟቸውን ጀብዶች አንድ ሁለት እያልን መቁጠር እንችላለን፡፡

በተከታታይ ሁለት የኦሎምፒክ መድረኮች (ሮም እና ቶክዮ) ያውም አድካሚ በሆነው የረጅም ርቀት የማራቶን ውድድር ወርቅ ማጥለቅን የእኛው ጀግና አበበ ቢቂላ እንጂ ማን ደፈረው? በአንድ የኦሎምፒክ መድረክ በ5ሺ እና በ10ሺ ሜትር ርቀት ድርብ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት መሆንን ለዓለም ያስተማረውም የእኛው ምሩፅ ይፍጠር ነው፡፡ በስፔን ዋና ከተማ በባርሴሎና ተዘጋጅቶ በነበረው ኦሎምፒክ በ10 ሺ ሜትር ተወዳድራ የመጀመሪያዋ ጥቁር አፍሪካዊት የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ የሆነችው ኢትዮጵያዊቷ ደራርቱ ቱሉ ናት፡፡ ደራርቱ ይህንን ድል አስመዝግባ ወደ አገሯ እንደተመለሰች የሻለቅነት ማዕረግ አግኝታለች፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥም በስሟ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሰይሞላታል፡፡

ሀ. በአንድ የኦሎምፒክ መድረክ በ5ሺ እና በ10ሺ ሜትር ርቀት ድርብ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤትነትን ለዓለም ያስተማረው ማን ነው?

ለ. የእነዚህን አትሌቶች ፈለግ በመከተል የቀጠሉት አትሌቶች እነማን ይመስሏችኋል?

ይህንን ፈለግ ተከትሎ ታሪክ ቢደገምም በኛው ልጆች በእነ ኃይሌ ገ/ስላሴ፣ በእነ ቀነኒሳ በቀለ፣ በእነ ጥሩነሽ ዲባባ፣ በእነ መሠረት ደፋርና ሌሎችም ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ነው፡፡

ኃይሌ ገብረስላሴ በአትላንታ(1988) እና በሲድኒ(1993) ኦሎምፒያዶች በ10ሺ ሜትር ውድድር ላስገኛቸው የወርቅ ሜዳሊያዎች የድል ተምሳሌትነቱን ለማሳየት በአዲስ አበባ ትልቅ ጎዳና በስሙ ተሰይሞለት ይገኛል፡፡ ኃይሌ ተደጋጋሚ ድሎችን ለማግኘት በምክንያትነት የሚጠቅሰው ለአገሩ ሕዝብ ከፍተኛ ፍቅርና አክብሮት ስላለው ከሕዝቡ በየጊዜው የሚያገኘው ድጋፍ ይበልጥ እንዲተጋና እንዲበረታ ስለሚገፋፋው እንደሆነ ይናገራል፡፡

ሌላው ታላቁ የረጅም ርቀት ሯጭ ቀነኒሳ በቀለ በ5ሺ እና በ10ሺ ሜትር የተለያየ የዓለም አቀፍ እና የኦሎምፒክ ክብረወሰኖች ባለቤትና ታዋቂ አትሌት ነው፡፡ ቀነኒሳ በቀለ በአቴንስ

ኦሎምፒክ በ5ሺ. ሜትር፣ በቤጂንግ ኦሎምፒክ ደግሞ በ5ሺ. እና በ10ሺ. ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት ነው፡፡

ሌላዋ የ5ሺ. እና የ10ሺ. ሜትር የኦሎምፒክ ውድድር አሸናፊዋ ድንቋ አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ ናት፡፡ ጥሩነሽ ዲባባ የቤጂንግ ኦሎምፒክ የ10ሺ. ሜትር ክብረወሰን ሰብራለች፡፡ በዚሁ የኦሎምፒክ ውድድር በ5ሺ. እና በ10ሺ. ሜትር ሁለት የወርቅ ሜዳሊያ በማግኘት ታላቅና አስደናቂ አትሌት ለመባል በቅታለች፡፡ አዲስ አበባ ውስጥም በስሟ ሆስፒታል ተሰይሞላታል፡፡

መሠረት ደፋርም በአቴንስ ኦሎምፒክ በ5ሺ. ሜትር ውድድር በአስደናቂ ብቃት በአንደኝነት መፈፀም የቻለች እና ብቃቷን ያስመዘገበች ጀግና አትሌት ናት፡፡ ይህንኑ ብቃቷንም በሎንደን ኦሎምፒክም ደግማዋለች፡፡

(ምንጭ:- ሺ.በሺ. ለማ፤ አርዓያዎቹ 2007ዓ.ም ለንባብ ትምህርት እንዲያመች ተሻሽሎ የተወሰደ)

**መምህር:**

- "**የኦሎምፒክ ወርቆች**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በተመጠነ የድምጽ ደረጃ እና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን መሰረት አድርጎ የቀረበላቸውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ቃላት

**መምህር:**

- "**የኦሎምፒክ ወርቆች**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በተመጠነ የድምጽ ደረጃ እና ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ስለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያግዟቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ምንባቡን መሰረት አድርጎ የቀረበላቸውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

ሰዋስው

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቅጥያዎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች የመድረሻ ቅጥያን በመጠቀም ቃላትን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ተማሪዎች ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር በማጣመር ባለቅጥያ ቃላትን በሚመሰርቱበት ጊዜ ቅጥያዎችን ከቃላቱ ጋር በሚገባ ሰዋሰዋዊ ስርዓት እያዋሃዱ መጻፋቸውን ይከታተሉ፣ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቅጥያዎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው ፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎችን በጥንድ ወይም በቡድን (ከ4/6 ተማሪ ባልበለጠ) ያደራጇቸው፤ በጋራም እንደዲሰሩ ያበራታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ተማሪዎች የመድረሻ ቅጥያን በመጠቀም ቃላትን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤ በሚሰሩበትም ጊዜ ይደግፏቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ለ. ባለቅጥያ ቃላት መመስረት መልሶች፡፡

1. - ነት ፣ - ኦች = ደግነት ፣ ደጎች
2. - ኣማ = አሸዋማ
3. - ኧኛ ፣ - ኦች = ነገረኛ ፣ ነገሮች
4. - ኦች = ድመቶች
5. - አዊ = ኢትዮጵያዊ
6. - ዎች = ጫማዎች
7. - ነት = በጎነት
8. - ኣማ ፣ - ዎች = ተራራማ ፣ ተራራዎች
9. - ኧኛ ፣ - ኦች = ተንኮለኛ ፣ ተንኮሎች
10. -ኣዊ ፣ - ኦች = ሰማያዊ ፣ ሰማዮች

## ጽህፈት

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎች ስለዓረፍተነገር ምንነት የተማሩትን እንዲያስታሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ የተሰጡትን አዳዲስ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድጉ፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ❖ በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ንባብ

### የኢትዮጵያ የስፓርት አባት

**መምህር፡**

- ➢ በተማሪ መጽሐፍ ላይ **"የኢትዮጵያ የስፓርት አባት"** በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት ቀደምት ዕውቀታቸውን በመጠቀም የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ➢ ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- ➢ **"የኢትዮጵያ የስፓርት አባት"** በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡
- ➢ በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ለእነዚህ ተማሪዎች ለብቻቸው እርስዎ ያንብቡላቸው፡፡
- ➢ ተማሪዎች ለድህረ ንባብ የቀረቡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

**መምህር:**

- ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) **"የኢትዮጵያ የስፓርት አባት"** የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ለብቻቸው ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ስለተመሳሳይ እና ተቃራኒ ቃላት የተማሩትን በተለያዩ ስልቶች እንዲያስታውሱ ያድርጉ፤

### ሀ. የቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ መልሶች፡፡

| | ቃላት | ተመሳሳይ ፍቺ | ተቃራኒ ፍቺ |
|---|---|---|---|
| **ምሳሌ** | አሸነፈ | ድል አደረገ | ተረታ |
| 1 | ሁልጊዜ | ዘወትር | አልፎ አልፎ |
| 2 | መፈለግ | መሻት/መመኘት | መተው |
| 3 | በፊት | ቀድሞ | ኋላ |
| 4 | መዘዋወር | መንቀሳቀስ | ባለበት መሆን/መርጋት |
| 5 | ማግኘት | ማሳካት/ማምጣት | ማጣት |
| 6 | ውጤት | ስኬት | ሽንፈት |

**መምህር:**

- ተማሪዎች ስለቃላት ፍቺ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው ያበረታቷቸው፤
- ተማሪዎች በተሰጣቸው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃት አገባባዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡
  - በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## አቀላትፎ ማንበብ

***መምህር፡***

- ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ባሉ ምዕራፎች ለአቀላጥፎ ንባብ የንባብ ትክለኛነትን እንዲለማመዱ ተደርጓል፡፡ **በዚህ ምዕራፍ ደግሞ** ተማሪዎች ቃላትን በሚገባ ወይም **ትክክለኛነትን** ተክትለው ከማንበብ በዘለለ ተገቢውን ፍጥነት በመጠበቅ እንዲያነቡ በማድረግ ንባብን እንዲያዳብሩ ያድርጓቸው፡፡
- በተማሪ መጽሀፍ ላይ **"አንድ ብልህ ዐይነ-ስውር"** በሚል ርዕስ የቀረበውን አንቀጽ ተማሪዎች በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) በተናጠል በመደጋገም እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ባሉበት ሆነው ተራ በተራ ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ እና እርስ በእርስ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች በሚሰጧቸው ደቂቃ ውስጥ ከጓደኞቻቸው ፊት በመሆን **"አንድ ብልህ ዐይነ-ስውር"** የሚለውን አንቀጽ ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ተገቢውን **የንባብ ፍጥነት** ተከትለው ማንበባቸውን ይከታተሉ፤ ማስታወሻዎችንም በመያዝ በተገቢው የፍጥነት ደረጃ ያላነበቡ ተማሪዎችን የሚደግፉበት ስልት በመቀየስ የንባብ ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ ይደግፏቸው፡፡
- ተማሪዎች በተሰጣቸው ደቂቃ ውስጥ በትክክል ማንበባቸውን ይከታተሉ ማበረታቻም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ንባቡን እንዲያዳምጡ በማድረግ የምንባቡ ሃሳብ ስለምን እንደሆነ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓረፍተ ነገር ምንነት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች የተለያዩ ሃሳቦችን በዓረፍተነገር እንዲገልጹ ያድርጉ፤
- በሚያነሱት ሃሳብ (በሚናገሩት ዓረፍተነገር) ውስጥ ባለቤት (ድርጊት ፈጻሚ)፣ ተሳቢ(ድርጊት ተቀባይ "በሚናገሩት ዓረፍተነገር ውስጥ ተሳቢ ከተጠቀሙ") እና ግስ (የሃሳባቸው መቋጫ የሆነ ማሰሪያ አንቀጽ መሆኑን) ቃላቶቹን እየጠሩ ያስረዷቸው፡፡
- እርስዎም ባለቤት፣ ተሳቢና ግስን በመጠቀም ዓረፍተነገር በመመስረት ተማሪዎች በዓረፍተነገሩ ውስጥ ያለውን ባለቤት፣ ተሳቢ እና ግስ እንዲለዩ ያድርጉ፡፡

  ምሳሌ፡- **ተማሪው በሩን ከፈተ፡፡** **ባለቤት፡-** ተማሪው፤ **ተሳቢ፡-** በሩ ፤ **ግስ፡-** ከፈተ መሆኑን ያስረዷቸው፡፡
- ስለዓረፍተ ነገር ክፍሎች የተዘጋጀውን ማስታወሻ ይጻፉላቸው፡፡
- የተዘጋጀውን ማስታወሻ በክፍል ደረጃቸው በሚመጥን መልኩ ይስጧቸው፤ ያስረዷቸው

## የዓረፍተነገር ክፍሎች

መሠረታዊ የሚባሉት የዓረፍተነገር ክፍሎች ባለቤት፣ ተሳቢ እና ማሰሪያ አንቀፅ ናቸው፡፡ በአንድ በተሟላ ዓረፍተነገር ውስጥም ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ (ግስ) የግድ ናቸው፡፡ ተሳቢ ግን እንደሁኔታው ሊኖርም ላይኖርም ይችላል፡፡

1. **ባለቤት** ፡- ባለቤት የሚባለው በዓረፍተነገር ውስጥ ድርጊት ፈጻሚው ነው፡፡

ምሳሌ፡- ቅዱስ መጽሐፍ አነበበ፡፡ (በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ድርጊቱን የፈጸመው ቅዱስ ነው፡፡ ስለዚህ
የዓረፍተ ነገሩ በለቤት "**ቅዱስ**" ነው፡፡)

**መምህር፡**

2. **<u>ተሳቢ</u>፡-** በዓረፍተነገር ውስጥ ድርጊት የተፈፀመበት (ድርጊት ተቀባይ) ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** አንበሳው ሚደቋዋን ገደላት፡፡ (በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ድርጊቱ የተፈጸመበት (ድርጊት ተቀባይ) ሚዳቋዋ ናት፡፡ ስለዚህ የዓረፍተነገሩ ተሳቢ "**ሚዳቋዋ**" የሚለው ነው)

3. **ማሰሪያ አንቅጽ**(ግስ)፡- ከዓረፍተነገር መጨረሻ በመግባት የዓረፍተነገሩ ማሰሪያ (መቋጫ) በመሆን የሚያገለግል የቃል ክፍል ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** ኡስማን ወደ ቤቱ <u>ሄደ</u>፡፡ (በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ድርጊቱን የሚያሳየው ቃል ሄደ የሚለው ነው፡፡ ስለዚህ **ሄደ** የዓረፍተነገሩ ሃሳብ መቋጫ ግስ (ማሰሪያ አንቀጽ ነው፡፡ )

- በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኝን ባለቤት ለማወቅ "ማን<u>    +   (ግስ)</u>?" ፤ ተሳቢ ለማወቅ "ምን<u> + (ግስ)</u>?" በማድረግ ማግኘት እንችላለን፡፡

**ምሳሌ፡-** አናጢው ሚስማር መታ፡፡

- ባለቤቱን ለማግኘት፡- ማን መታ? አናጢው (ይህ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው፡፡)
- ተሳቢውን ለማግኘት፡- ምን መታ? ሚስማር (ይህ የዓረፍተነገሩ ተሳቢ ነው፡፡)
- ግሱን ለማግኘት፡- በዓረፍተ ነገር ውስጥ የምን ድርጊት ተከናወነ ወይም ሃሰቡ በምን ተቋጫ ብለን ስንፈልግ የምናገኘው ግስ (ማሰሪያ አንቀጽ ይባላል፡፡)

- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ሰዋስው

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓፍተነገር ክፍሎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው።
- ተማሪዎች ስም እና ግስን እንዲለዩ በቅድሚያ የተሰጡትን ምሳሌዎች በሚገባ እንዲረዱ ያድርጉ፤ በተጨማሪም ምሳሌዎችን በመስጠት ያሰሯቸው፤ ያስረዷቸው።
- ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያስረዷቸው፤ ይደግፏቸው፤

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓፍተነገር ክፍሎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው።
- ተማሪዎች በዓረፍተነገሮቹ ውስጥ ያሉትን ባለቤቶች እንዲለዩ በቅድሚያ የተሰጡትን ምሳሌዎች በሚገባ እንዲረዱ ያድርጉ፤ በተጨማሪም ምሳሌዎችን በመስጠት ያሰሯቸው፤ ያስረዷቸው።
- ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያስረዷቸው፤ ይደግፏቸው፤

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓፍተነገር ክፍሎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው።
- ተማሪዎች በዓረፍተነገሮቹ ውስጥ ያሉትን ተሳቢዎች እንዲለዩ በቅድሚያ የተሰጡትን ምሳሌዎች በሚገባ እንዲረዱ ያድርጉ፤ በተጨማሪም ምሳሌዎችን በመስጠት ያሰሯቸው፤ ያስረዷቸው።

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓፍተነገር ክፍሎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡

- ተማሪዎች በዓረፍተነገሮቹ ውስጥ ያሉትን ግሶች እንዲለዩ በቅድሚያ የተሰጡትን ምሳሌዎች በሚገባ እንዲረዱ ያድርጉ፤ በተጨማሪም ምሳሌዎችን በመስጠት ያሰሯቸው፤ ያስረዷቸው፡፡

- ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያስረዷቸው፤ ይደግፏቸው፤

**መምህር፡**

- ተማሪዎች በዓረፍተነገር ውስጥ ስለባለቤት እና ግስ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፡፡

- ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን (ከ4/6 ተማሪዎች) ባልበለጠ እንዲቀመጡ ያድርጉ፤

- ተማሪዎች በተሰጧቸው ዓረፍተነገሮች ውስጥ የባለቤት እና የግስ ስህተት መኖሩን ወይም አለመኖሩን  እንዲለዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ያሰሯቸው፤ ያስረዷቸው፡፡
- ተማሪዎች ስህተት ያለባቸውን አረፍተ ነገሮች ከለዩ በኋላ ስህተቶቹን ምን እንደሆኑ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያስረዱ ያበረታቷቸው፡፡

- ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያስረዷቸው፤ ይደግፏቸው፤

**መምህር፡**

- ተማሪዎች በዓረፍተነገር ውስጥ ስለባለቤት እና ግስ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በተሰጧቸው ዓረፍተነገሮች ውስጥ የባለቤት እና የግስ ስህተት መኖሩን ወይም አለመኖሩን እንዲለዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ያሰሯቸው፤ ያስረዷቸው፡፡
- ተማሪዎች በዓረፍተነገሮቹ ውስጥ ያሉትን የባለቤት እና የግስ ስምምነት ስህተት ያለባቸውን በማስተካከል በድጋሚ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያስረዷቸው፤ ይደግፏቸው፤

✍ ጽህፈት

መምህር፡

- ❖ ተማሪዎች ቀደምት ዕውቀታቸውን በመጠቀም ስለ ውይይት ምንነት እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው።
- ❖ ተማሪዎች በውይይት እና ክርክር መሃል ያውን አንድነት እና ልዩነት እንዲናገሩ ያበረታቷቸው።
- ❖ ስለአንቀጽ ውይይት የተዘጋጀውን ማስታወሻ ይጻፉላቸው።
- ❖ ተማሪዎችም ማስታወሻውን በሚገባ እንዲጽፉ ያድርጉ፤ ያብራሩላቸውም።

## ውይይት

ውይይት የምንለው ሰዎች አንድና ከአንድ በላይ በሆኑ ርዕሰ ጉዳች ዙሪያ ሐሳብ የሚለዋወጡበትና የጋራ መግባባት ላይ የሚደርሱበት ተግባር ነው።

### የውይይት ዝግጅት

- ✓ የውይይት ርዕሱን በተመለከተ መረዳት
- ✓ ርዕሱን በተመለከተ መረጃ አፈላልጎ መያዝ
- ✓ መረጃዎቹ ለተሳታፊዎቹ የሚመጥኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ

### የውይይት አቀራረብ

- ✓ አለባበስንና ንጽህናን ጠብቆ መገኘት
- ✓ የውይይቱን አላማ ማቅረብ
- ✓ ተራን ጠብቆ መናገር
- ✓ የሌሎችን ሐሳብ ማክበር
- ✓ የተመጠነ ሐሳብ ማቅረብ
- ✓ ድምፅን መመጠን
- ✓ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መቀበልና ምላሽ መስጠት።

- ❖ በክርክር እና በውይይት መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ መረዳታቸውን ያረጋግጡ፤
- ❖ ማስታወሻውን በክፍል ደረጃቸው ልክ በተለያዩ ስልቶች ተማሪዎችን በማሳተፍ ያብራሩላቸው።
- ❖ ተማሪዎች በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ውይይት ከማድረጋቸው በፊት በቅድሚያ በቡድን እንዲሆኑ በማድረግ ስለተወሰኑ አትሌቶች መረጃ ቀድመው እንዲሰበስቡ ያዘጋጇቸው።

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎች ስለ ውይይት ምንነት እና መመሪያ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበራታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች በተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ መሰረት መረጃዎችን በመያዝ ነጻ ውይይት እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በተማሩት መሰረት ውይይቱን ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይከታተሉ፤ ድጋፍም ያድርጉላቸው፡፡

## የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ

**መምህር**

ተማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የምዕራፉን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ መረዳታቸውን በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተቀመጡትን የምዕራፉን ማጠቃለያ ጥያቄዎች እንዲሰሩ በማድረግ ያረጋግጡ፤ እንዲሁም ከምዕራፉ ይዘት ጋር የሚገናኙ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመስጠት የምዕራፉን ትምህርት ያጠቃሉ፡፡

- ✓ በዚህ ምዕራፍ ስር አዳምጦ እና አንብቦ የመረዳትን፣ የመናገር እና የጽህፈት ክሂሎችን አዳብረዋል፡፡
- ✓ ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍቺ ሰጥተዋል፡፡
- ✓ ቅጥያዎችን ከዋና ቃል መነጠል እና ማጣመር ችለዋል፡፡
- ✓ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የባለቤት፣ ተሳቢ እና የማሰሪያ አንቀጽ ምንነትን ለይተዋል፡፡
- ✓ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የባለቤት እና የግስ መስማማትን ለይተው አውቀዋል፡፡
- ✓ የቡድን ውይይት ምንነት እና መመሪያን አውቀዋል፡፡
- ✓ የውይይት መመሪያን በመከተል ውይይት ማድረግ ችለዋል፡፡

# ምዕራፍ ሰባት (፯)

## ውሃ

**የተሰጠ ክፍለ ጊዜ 9**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ኢ-መደበኛ በሆነ አደረጃጀት በሚና ጨዋታ ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡
- አዳምጠው የጽሁፉን ሃሳብ በዝርዝር ይገልጻሉ፡፡
- በራሳቸው የተሟላ አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- ገላጮችን በመጠቀም አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- መዝሙር አዳምጠው ስለ ውሃ ጥቅም ይጽፋሉ፡፡
- በተሰጣቸው ርእስ ክርክር ያደርጋሉ፡፡
- በተሰጣቸው ግስ የተሟላ አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ማዳመጥ እና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መጻፍ
- ሰዋስው

 ማዳመጥ

## ውሃ ምንድን ነው?

**መምህር፡**

- **"ውሃ ምንድን ነው?"** የሚለውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡
- የዝግታ ንባብ ስልትን በመጠቀም ምንባቡን በእርጋታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡

  ✓ **የዝግታ ንባብ የምንለው ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ጠለቅ ያለ ማብራሪያ እና ምላሽ ለመስጠት የሚረዳ የንባብ ዓይነት ነው፡፡**
- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ቀድመው ምንባቡን ኮፒ አድርገው በመስጠት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ በሚገባ እያዳመጡ መሆናቸውን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያረጋግጡ፤
- ተማሪዎች የተዘጋጀውን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፤

### ውሃ ምንድን ነው?

ውሃ በዕለት ተዕለት ኑሯችን እንደ ምግብና አየር መሰረታዊ ፍላጎታችን ነው፡፡ ውሃ ምንድን ነው? ለሚለውም ጥያቄ መልስ ሊሆነን የሚችለው ፍቺ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ለመጠጥ፣ ለንጽህና መጠበቂያ፣ ለምግብ ማብሰያ. . . የምንጠቀምበት ፈሳሽ ውሃ ይባላል፡፡

የቧንቧ ውሃን ወይም የምንጭ ውሃን በብርጭቆ ወስደን ብንመለከተው ምንነቱን በግልጽ መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም ውሃ በውስጡ ሌሎች ነገሮችን ማሳየት ያስችላል፤ እንዲሁም ውሃ መያዣ ያስፈልገዋል፤ ቀለም ፣ ሽታና ጣዕም የለውም፡፡

ሰዎች ውሃን ከወንዝ፣ ከጉድጓድ፣ ከምንጭ፣ ከሐይቅና ከዝናብ ያገኛሉ፡፡ እነዚህ የውሃ መገኛ አካላት ይባላሉ፡፡ በአብዛኛው በከተማ የሚኖሩ ሰዎች የቧንቧ ውሃን ይጠቀማሉ፡፡ የውሃ አካላት በውስጣቸው በያዙት የማዕድናት (ንጥረ-ነገሮች) ብዛት ንጹህ ውሃና ጨዋማ ውሃ በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡

ሀ. ዉሃ ምንድን ነው?

ለ. ንጹህ እና ጨዋማ ውሃ የሚባሉት የትኛዎቹ ይመስላችኋል?

ከወንዝ፣ ከጉድጓድ፣ ከምንጭ፣ ከኩሬና ከዝናብ የሚገኝ ውሃ ንጹህ ውሃ ይባላል፡፡ ንጹህ ውሃ በውስጡ ማዕድናት (ጨው) የለውም፡፡ ቢኖረውም መጠኑ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ በተቃራኒው የባህር፣ የውቂያኖስና የአንዳንድ ሐይቆች ውሃ ጨዋማ ውሃ ይባላል፡፡ በእነዚህ የውሃ አካላት ውስጥ የሚገኘው የጨው መጠን በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ከጨው ሌላ ማዕድናትንም ሊይዝ ይችላል፡፡ ይህ ውሃ ለመጠጥና ለዕጽዋት ሊሆን አይችልም፡፡

ንጹህ ውሃ ለመጠጥ፣ ለንጽህና መጠበቂያና ለምግብ ማብሰያ ያገለግላል፡፡ ከዚህ ውጭ ውሃ በምግብ ማግኛ ቦታነት፣ በመዝናኛ ስፍራነት፣ ለትራንስፖርት መጓጓዣ ማዕከልነት እና ለኢንዱስትሪ ሥራዎች ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ውሃ ለእንስሳት በመኖሪያ ሥፍራነት፣ በመጠጥነት፣ በምግብ ማግኛነት እና በመንቀሳቀሻ አካባቢነት ያገለግላል፡፡

እጽዋትም ልክ እንደ እንስሳት ሁሉ ህይወት ስላላቸው ይተነፍሳሉ፤ ያድጋሉ፤ ምግብ ያዘጋጃሉ፤ ይመገባሉ፡፡ ከዘር ጀምረው አድገው ፍሬና ዘር እስከሚሰጡ ድረስ ውሃ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በመሆኑም ውሃ ለሰው ልጅ፣ ለእንስሳትና ለእፅዋት መሰረታዊ ነገር ነው፡፡

(ምንጭ፡- ብርሃኑ ሀብተማርያም፡፡ 1997፡፡ ውሃ ሕይወት ነው፡፡ (ለንባብ ማስተማሪያነት ተስማምቶ የቀረበ፡፡)

## ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቃላት አገባባዊ ፍቺ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡

  ምሳሌ፡- መምህር፡- በምህርሩ <u>በፍጥነት</u> መጣ፡፡ ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳዩን እንዲሰጡ ያበረታታቸው፡፡

  ተማሪዎች፡- መመህር <u>ቶሎ</u> መጣ፡፡. . . እያሉ እንዲመልሱ ተመሳሳይ ምስሰሌዎችነ ያሰሯቸው፡፡

- ተማሪዎች በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባዊ ፍቻቸውን እንዲለዩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያግዟቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡

- ተማሪዎች ለተሰጣቸው ቃላት በፍቺ ተቃራኒ ከሆኑት ጋር እንዲያዛምዱ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡

- ተማሪዎች ከተሰጣቸው ቃላት ውስጥ ሌላ ቃላትን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

  **ምሳሌ፡-** የቃላት ማስተማሪያ ቻርትን በመጠቀም ወይም በማዘጋጀት በመርጃ መሳሪያነት ይጠቀሙ፡፡

- ተማሪዎች የተሰጠውን ምሳሌ በሚገባ እንዲረዱ ያድርጉ፤ በተመሳሳይ ሌሎች ምሳሌዎችን በመስጠት ያስረዷቸው፡፡

## ሐ. ከቃላት ውስጥ ሌሎች ቃላትን መመስረት- መልሶች፡፡

- ተማሪዎች ከእነዚህ ቃላት በተጨማሪ ሌሎች ቃላትን ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡

1.

| | | |
|---|---|---|
| መመጣጠናቸው | ጠጣ | መጠጣቸው |
| | መጣ | ውጣ |
| | ጣመ | መጠናቸው |

2.

| | | |
|---|---|---|
| አሰባበረ | አሰበ | አበረ |
| | ሰበረ | አሰረ |
| | አረባ | አረሰ |

3

| | | |
|---|---|---|
| አመሰቃቀለ | ሰቀለ | አቀመሰ |
| | ለቀመ | አለቀሰ |
| | ቀሰመ | አለቀ |

4

| | | |
|---|---|---|
| ስለመሰከረለት | መለሰ | ሰመረ |
| | ሰከረ | መሰረት |
| | መከረ | መሰከረ |

## መናገር

**መምህር፡**

ከንጽህና አጠባበቅ ጋር የተያያዙ መዝሙሮችን በማዘጋጀት ተማሪዎች በጋራ እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

ልጆች ከንጽህና አጠባበቅ ጋር በተያያዘ የሚያውቁት ተጨማሪ መዝሙሮች ካሉ እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፤

**"ጤናችን በእጃችን"** የሚለውን የህጻናት መዝሙር ግጥም በእርጋታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡

- ✓ *የዝግታ ንባብ የምንለው ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ጠለቅ ያለ ማብራሪያ እና ምላሽ ለመስጠት የሚረዳ የንባብ ዓይነት ነው፡፡*

- ተማሪዎች ለግጥሙ ዜማ እዲያወጡ ዕድል ይስጧቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ግጥሙን በዜማ እና በእርጋታ ለተማሪዎች ይዘምሩላቸው፤
- ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ እና በመደጋገም ዜማውን ተከትለው እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው፡፡

**ጤናችን በእጃችን**

*ሥራዎን ሰርተው ሲጨራርሱ፤*
*በሳሙና እጅን መተጣጠቡን ፍጹም አይርሱ፡፡* } 2 ጊዜ

*በሳሙና እጅን ሳይታጠቡ፤*
*ሰውን መጨበጥ ዓይን ማሻሸት፤*
*አፍ መጠራረግ ሕጻን ልጅ ማጥባት፤*
*ወይ ምግብ መብላት፤*
*በሽታ ያመጣል በሰው ልጅ ሕይወት፡፡* } 2 ጊዜ

(ከላይ ያሉት ሁሉ) 2 ጊዜ

(ምንጭ፡- አርቲስት ስለሺ ደምሴ (ጋሽ አበራ ሞላ)

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎችን በቡድን (4/6 ተማሪዎች ባልበለጠ) በማድረግ ከግጥሙ የተረዱትን ሃሳብ በጽሁፍ እንዲያስቀምጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በውይይታቸው መሰረት ስለግጥሙ የጻፉትን ሃሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡
- ❖ በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ በቅድሚያ ግጥሙን ጎፒ አድርገው ይስጧቸው
- ❖ ተማሪዎች ስለ ውሃ አጠቃቀም እና . . . ከውሃ ጋር በተያያዘ የራሳቸውን ቀለል ያለ ጭውውት ወይም መዝሙሮችን ቀድመው እንዲያዘጋጁ በቡድን በማደራጀት ኃላፊነት ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎች በየቡድናቸው ያዘጋጁቸውን አጫጭር ጭውውቶች ወይንም መዝሙሮች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡

## ጽህፈት

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎች ስለዓረፍተነገር እና ስለአንቀጽ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎችን በጥንድ ወይም በቡድን (ከ4/6 ተማሪዎች ባልበለጠ) እንዲሆኑ በማድረግ የተሰጣቸውን ዓረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተል በማተካከል አንቀጽ እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- ❖ በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

### ሀ. የተዘበራረቁ ዓረፍተነገሮች ቅደም ተከተላቸውን በማስተካከል አንድ አንቀጽ መጻፍ መልስ፡፡

ኡፋይሴ ዘወትር ትምህርትቤት ከመሄዷ በፊት የተለያዩ ተግባራትን ታከናውናለች፡፡ ከእነዚህ ተግባራት መካከል በጠዋት ተነስታ አልጋዋን ካነጠፈች በኋላ ፊቷን በውሃና ሳሙና ትታጠባለች፡፡ ከዛም የደንብ ልብሷን ለብሳ የተዘጋጀላትን ቁርስ ትበላለች፡፡ ቀጥሎም ማታ ላይ ያዘጋጀችውን ደብተሮች በቦርሳ ይዛ እናቷን ተሰናብታ ከአባትዋ ጋር ጉዞ ትጀምራለች፡፡ አባቷም ትምህርትቤቷ በር ላይ እደደረሱ ስመው ይለዩታል፡፡ እሷም ወደ ትምህርትቤት ትገባለች፡፡

## ንባብ

### ከሰከላ እስከ ጉባ

**መምህር፡**

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ **"ከሰከላ እስከ ጉባ"** በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት ቀደምት ዕውቀታቸውን በመጠቀም የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- **"ከሰከላ እስከ ጉባ"** በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ለእነዚህ ተማሪዎች ለብቻቸው እርስዎ ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ለድህረ ንባብ የቀረቡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

### ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) **"ከሰከላ እስከ ጉባ"** የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ለብቻቸው ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ስለተመሳሳይ እና ተቃራኒ ቃላት የተማሩትን በተለያዩ ስልቶች እንዲያስታውሱ ያድርጉ፤
- በምንባቡ መሰረት ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
  - በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

ሀ. "ከሰከላ እስከ ጉባ" በሚለው ምንባብ መሰረት የቃላት ተቃራኒ ፍቺ መልስ፡፡

1. ተለያይተው
2. ጥቂት
3. ማስቀጠል
4. በረታ
5. ጉዳት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) **"ከሰከላ እስከ ጉባ"** የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ለብቻቸው ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡
- ተማሪዎች ስለተመሳሳይ እና ተቃራኒ ቃላት የተማሩትን በተለያዩ ስልቶች እንዲያስታውሱ ያድርጉ፤
- በምንባቡ መሰረት ለቃላት አገባባዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

  - በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ጽህፈት

**መምህር:**

- ተማሪዎች ስለዓረፍተነገር የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው ያበረታቷቸው፤
- ተማሪዎች በተሰጧቸው ቃላት ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው።

**መምህር:**

- ተማሪዎች በቀጣይ ክፍለ ጊዜ በሚሰጣቸው ርዕስ ላይ ክርክር እንዲያደርጉ ቀድመው ርዕስ ይስጧቸው።

  ምሳሌ፡- ውሃ በይበልጥ ለእንስሳት ያስፈልጋል

  ውሃ በይበልጥ ለእጽዋት ያስፈልጋል

- ርዕሱን በዕጣ ይስጧቸው፤

## ንግግር

**መምህር:**

- ተማሪዎች ስለክርክር ምንነት እና መመሪያዎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው።
- ተማሪዎች በተዘጋጁበት የመከራከሪያ ርዕስ ላይ በሰበሰቡት መረጃ መሰረት ክርክሩን እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው።
- ተማሪዎች ክርክሩን በሚያከናውኑበት ወቅት ሙሉ የክርክር መመሪያዎችን እና ስርዓትን ተከትለው እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው ፤ ድጋፍም ያድርጉላቸው፤

## ሰዋስው

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለገላጭ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በዓረፍተነገሮች ውስጥ የተለያዩ የስም ገላጭ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተነገሩን እንዲያሟሉ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

ምሳሌ፡- የቃል ክፍሎችን ማስተማሪያ ቻርትን በመጠቀም ማስተማር ይችላሉ፡፡

- ተማሪዎች ከተለያዩ ቃላት ውስጥ ግሶችን እንዲለዩ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ስለግስ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

### ሐ. በሳጥኑ ውስጥ ከተዘረዘሩት ቃላቶች መካከል ግስ የሆኑ ቃላት መልሶች፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ተነሳ | 3. ሮጠ | 5. አሸነፈ | 7. አጸዳ | 9. ቀባች |
| 2. ነው | 4. አደገ | 6. ቆረጠ | 8. አነበበ | 10 አበሰ |

### ጽህፈት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለግስ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ጅምር ዓረፍተነገሮችን ግስ በመጠቀም እንዲያሟሉ ምሳሌዎችን በመስጠት ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለግስ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በተሰጣቸው ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ግሶችን እንዲለዩ እና ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱባቸው ምሳሌዎችን በመስጠት ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያንበብቡላቸው፤ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ባሉ ምዕራፎች ለአቀላጥፎ ንባብ የንባብ ትክለኛነትን እንዲለማመዱ ተደርጓል፡፡ **በዚህ ምዕራፍ ደግሞ** ተማሪዎች ቃላትን በሚገባ ወይም **ትክክለኛነትን** ተክትለው ከማንበብ በዘለለ ተገቢውን ፍጥነት በመጠበቅ እንዲያነቡ በማድረግ ንባብን እንዲያዳብሩ ያድርጓቸው፡፡
- በተማሪ መጽሀፍ ላይ "**አህያ እነ በሬ**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሁፍ ተማሪዎች በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) በተናጠል በመደጋገም እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች ባሉበት ሆነው ተራ በተራ ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ እና እርስ በእርስ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች በሚሰጧቸው ደቂቃ ውስጥ ከጓደኞቻቸው ፊት በመሆን "**አህያ እና በሬ**" የሚለውን ጽሁፍ ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች ከተማሪዎች ፊት ወጥተው ከማንበባቸው በፊት ባሉበት ሆነው እርስ በእርስ ስለንባባቸው እንዲተራረሙ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ተገቢውን **የንባብ ፍጥነት** ተከትለው ማንበባቸውን ይከታተሉ፤ ማስታወሻዎችንም በመያዝ በተገቢው የፍጥነት ደረጃ ያላነበቡ ተማሪዎችን የሚደግፉበት ስልት በመቀየስ የንባብ ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ ይደግፏቸው፡፡

በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ንባቡን እንዲያዳምጡ በማድረግ የምንባቡ ሃሳብ ስለምን እንደሆነ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡

## የምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ

**መምህር**

ተማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የምዕራፉን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ መረዳታቸውን በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተቀመጡትን የምዕራፉን ማጠቃለያ ጥያቄዎች እንዲሰሩ በማድረግ ያረጋግጡ፤ እንዲሁም ከምዕራፉ ይዘት ጋር የሚገናኙ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመስጠት የምዕራፉን ትምህርት ያጠቃሉ፡፡

- ✓ በዚህ ምዕራፍ ስር አዳምጦ እና አንብቦ የመረዳትን፣ የመናገር እና የጽህፈት ክሂሎችን አዳብረዋል፡፡
- ✓ ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍቺ ሰጥተዋል፡፡
- ✓ ገላጮችን ከሌሎች ቃላት መለየት ችለዋል፡፡
- ✓ ገላጮችን በዓረፍተነገር ውስጥ በመጠቀም አሳይተዋል፡፡
- ✓ በተሰጣቸው ርዕስ የክርክር መመሪያዎችን ተከትለው ክርክር አድርገዋል፡፡
- ✓ ግሶችን ከሌሎች ቃላት መለየት ችለዋል፡፡
- ✓ ግሶችን በዓረፍተነገሮች ውስጥ በመጠቀም አሳይተዋል፡፡

# ምዕራፍ ስምንት (፰)

## መደራደር

**የተሰጠ ክፍለ ጊዜ 9**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- አዳምጠው ተራ በተራ በንግግር ይሳተፋሉ፡፡
- በግላቸው አንብበው ዝርዝሩን ያብራራሉ፡፡
- የትምህርት ቤታቸውን ህግና ደንብ ይጽፋሉ፡፡
- ቅጥያዎችን ከቃላት ላይ ይነጥላሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ማዳመጥ እና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መጻፍ
- ሰዋስው



### ማዳመጥ

### ትሁቷ ፋሲሌ

**መምህር፡**

- **"ትሁቷ ፋሲሌ?"** የሚለውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡
- ምንባቡን **የዝግታ ንባብ ስልትን** በመጠቀም በእርጋታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ቀድመው ምንባቡን ኮፒ አድርገው በመስጠት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ በሚገባ እያዳመጡ መሆናቸውን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያረጋግጡ፡፡
- ተማሪዎች የተዘጋጀውን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## ትሁቷ ፋሲሌ

ፋሲሌ በትምህርቷ ጎበዝ፣ በስነ-ምግባሯም ትሁት ልጅ ናት፡፡ የትምህርት ቤት ጓደኞቿ ሲቀ-ትሁት የሚል ቅፅል ስም ሰጥተዋታል፡፡ ስያሜውን የሰጧት ካላት ጥሩ ባህሪና ጉብዝና በመነሳት እንደሆነም ይናገራሉ፡፡ ፋሲሌ በሰዎች መካከል የሚፈጠር የሃሳብ ልዩነትንና ቅያሜን በድርድር መፍታት እንደሚገባ በምታገኘው አጋጣሚ ሁሉ ታስተምራለች፡፡ ዘወትር ሰኞ ሰኞ በሰንደቅ-አላማ ስነ-ስርዓት ላይ ለትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በሙሉ ስለዚሁ ጉዳይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ትሰጣለች፡፡

ፋሲሌ እንደተለመደው አንድ ሰኞ ጠዋት በሰንደቅ-አላማ አከባበር ስነ-ስርዓት ላይ ስለድርድር ለማስተማር ወደመድረክ እያመራች እያለ ሁለት ተማሪዎች ተጣልተው ለድብድብ ሲጋበዙ ተመለከተቻቸው፡፡

ሀ. በሰዎች መካከል ልዩነት ሲፈጠር በምን መንገድ መፍታት ይቻላል?

ለ. ጓደኞቻችሁ ተጣልተው ብታገኙ ምን ታደርጋላችሁ?

ያየችውን ለትምህርትቤቱ ርዕሰ መምህር በመንገር እየተጣሉ ያሉ ተማሪዎችን ለመገላገል በፍጥነት ወደእነሱ አመራች፡፡ ልጆቹ ጋር እንደደረሰች መጣላት ከአንድ ስነ-ምግባር ካለው ተማሪ የሚጠበቅ እንዳልሆነና ችግሮችን በድርድር መፍታት እንደሚቻል አሳምና የተጣሉበትን ጉዳይም ሌሎች ተማሪዎች ይማሩበታል ብላ ስላሰበች ተማሪዎችና መምህራን በተሰበሰቡበት እንዲደራደሩ ዕድሉን ሰጠቻቸው፡፡

ከጓደኛሞቹ አንደኛው፡- "የጸባችን መነሻ ጓደኛዬ ያዋስኩትን መጽሀፍ ከተጠቀመበት በኋላ አመስግኖ እንደመመለስ ሌላ ጊዜ እንደማይጠቀምበት እና እንደአልባሌ ነገር ከሩቅ ሆኖ 'ያውልህ ውሰድ፡፡' ብሎ ሲወረውረው የመጽሀፉ ሽፋን ተቀደደ፡፡ በዚህ ጊዜ ተናድጄ ልመታው ስል እናንተ ደርሳችሁ አገላገላችሁን፡፡" በማለት መለሰ፡፡

ጓደኛውም እንዲህ አለ "የተናገረው ነገር እውነት ነው መጽሀፉን በስርዓት ወስጄ እንደተጠቀምኩበት ሁሉ ስመልስም በስርዓት መስጠት ሲኖርብኝ ባለሁበት ሆኜ በመወርወሬ መጽሀፉ እንዲቀደድ ምክንያት መሆኔን አልክድም፡፡ ሊጣላኝም ሲመጣ እኔም ለመደባደብ ተጋብዤለሁ፡፡ ቢሆንም ግን የዚህ ሁሉ ነገር መነሻ እኔ ስለሆንኩ በእናንተ ፊት ጓደኛዬን

ይቅርታ መጠየቅ እፈልጋለሁ። መጽሀፋንም በሚገባ አጣብቄ አስተካክልለታለሁ።" በማለት "ይቅርታ አርግልኝ።" ብሎ ጓደኛውን አቀፈው። ይቅርም ተባባሉ።

ፋሲሌ ልጆቹን በዚህ መልኩ እንዲደራደሩና የተጣሉበትን ጉዳይ በውይይት መፍታት እንዲችሉ አደረገች። የተሰበሰቡት ተማሪዎችና መምህራንም ልጆቹ የተስማሙበት መንገድ በጣም አስደሰታቸውና አጨበጨቡ። የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርም ፋሲሌ ላደረገችው ሁሉ አመስግነው የእለቱን መርሀ-ግብር የኢትዮጵያን ህዝብ ብሔራዊ መዝሙር በመዘመር ተጠናቆ ወደክፍል ገቡ።

## ቃላት

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎች ስለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያግዟቸው፤ ያበረታቷቸው።
- ❖ ተማሪዎች ለቃላት ተቃራኒ ፍች እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው።
- ❖ በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው።

## ጽህፈት

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎች ስለዓረፍተነገር የተማሩትን እንዲስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው።
- ❖ ተማሪዎች በተሰጣቸው ቃላት ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው።
- ❖ የሚከብዷቸው ቃላት ካሉ ትርጉማቸውን ይንገሯቸው።
- ❖ በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው።

## መናገር

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎች ንግግር ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ሃሳባቸውን እንዴት እንደሚገልጹ ይጠይቋቸው፡፡

ምሳሌ፡- - ስለትምህርትቤታቸው ሁኔታ
- ስለትምህር አስፈላጊነት
- ስለ ሰፈራቸው እና አካባቢያቸው ሁኔታ. . . እንዲናገሩ ወይንም ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡

- ❖ ተማሪዎች ከተናገሩ በኋላ በድጋሚ ንግግር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይጠይቋቸው፤ ለመልሶቻቸውም ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ ስለ ንግግር የተዘጋጀውን ማስታወሻ ይጻፉላቸው፤ ተማሪዎችም እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ❖ ማስታወሻውን በክፍል ደረጃቸው ልክ ብቻ ያብራሩላቸው፡፡

### ንግግር

ንግግር ማለት፡- አንድ ሰው በአዕምሮው ያሰበውን ነገር ለሌላ ሰው የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መግለፅ (ማሳወቅ) ማለት ነው፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች እናንተ ከጓደኞቻችሁ ጋር፣ ከወላጆቻችሁ ጋር፣. . ንግግር ማድረጋችሁ የተለመደ ነው፡፡ ሌላው ግን በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ ንግግር ሲደረግ እናያለን፡፡

ምሳሌ፡- መድረክ ላይ (ታዳሚዎች በሚገኙበት) የሚቀርብ ንግግር በሚከተሉት መመሪያዎች መሰርት ይዘጋጃል፤

**መምህር፡** የንግግር አዘገጃጀት

- ✓ የንግግር ርዕስ መምረጥ
- ✓ የንግግርን ርዕስ መወሰን (መመጠን)
- ✓ የንግግሩን ዓላማ በግልጽ መረዳት
- ✓ የአድማጭን ማንነት (ደረጃ) መለየት
- ✓ መረጃ ማሰባሰብ

የንግግር አቀራረብ

- ✓ አድማጭን በሚያረካ መንገድ ንግግር ማድረግ

✓ ንግግር በማቅረብ ሂደት ውስጥ የአድማጭን ሁኔታ መከታተል


✓ የንግግራችንን ዋና ዋና ነጥብ በማስታወስ ማጠቃለል

❖ ተማሪዎች በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ንግግር እንዲያደርጉ በቡድን በማድረግ ርዕሶችን ቀድመው በመስጠት በሚና ጨዋታ እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡

ምሳሌ፡- - የገበያ ስፍራን በማንሳት ገዢ እና ሻጭ

- በተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ቤተሰባዊ ውይይት
- የትምህርት አስፈላጊነት
- ሃገርን መውደድ
- በመርሃግብር ስለማጥናት ጥቅሞች
- ባህላዊ የልጆች ጨዋታ ዓይነቶች እና ሕጎቻቸው
- ስለ አንድነት እና መተባበር
- ስለ አካባቢ ጽዳት እነ ውበት

❖ (የሚቻል ከሆነ የተለየዩ ስልቶችን በመጠቀም በተማሪዎች የዕድሜ ደረጃ ልክ እና በማስተማሪያው ቋንቋ በልጆች የተዘጋጁ በተለየዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ንግግር ሲያደርጉ የሚያሳይ ድምጽና ምስል ከተገኘ ቀድመው ያሳዩቸው፡፡)



## ንባብ

## ድርድር

**መምህር፡**

➢ በተማሪ መጽሐፍ ላይ "**ድርድር**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት ቀደምት ዕውቀታቸውን በመጠቀም የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡

➢ ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

➢ "**ድርድር**" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

➢ በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ለእነዚህ ተማሪዎች ለብቻቸው

እርስዎ በዝግታ የንባብ ስልት ያንብቡላቸው፡፡

- ተማሪዎች ለድህረ ንባብ የቀረቡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ተመሳሰይ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- በምንባቡ መሰረት ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ተቃራኒ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ጽህፈት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓረፍተነገር የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው ያበረታቷቸው፤

  ምሳሌ ፦ ጻፈ፣ ተማረ. . . ቃላትን በመስጠት ተማሪዎች በቃል ተራ በተራ ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በተሰጧቸው ቃላት ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ሰዋስው

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቃት እና ቅጥያዎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡

**ምሳሌ፡-** ________________በስፖርት ሜዳ ላይ እየተጫወቱ ነው፡፡ (ተማሪ/ተማሪዎች)

ተማሪዎች ከተሰጣቸው ቃላት ውስጥ የዓረፍተ ነገሩን ሃሳብ በሚገባ የሚያሟላውን ቃል ተጠቅመው ዓረፍተነገሩን በድጋሚ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

- ተመሳሳይ ምሳሌዎችን በመስጠት መረዳታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የተዘጋጀውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች የተለየዩ አገላለጾችን እንዲረዱ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያበረታቷቸው፡፡

**ምሳሌ፡-** ለሀኪም አከመ ካልን ለመምህር ______________እንላለን፡፡ (አስተማረ)

ቆርቆሮ መታ ካልን ግንብ ____________እንላለን፡፡ (ገነባ)

ቅጠል ቀነጠሰ ካልን ዛፍ______________እንላለን፡፡ (ቆረጠ)

ስዕል ተመለከተ ካልን ሙዚቃ ______________እንላለን፡፡ (አዳመጠ)

ወጥ ተሰራ ካልን አብሲት______________እንላለን፡፡ (ተጣለ)

- በተመሳሳይ ሌሎች ምሳሌዎችን በመስጠት መረዳታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ተማሪዎች የሚሰጡትን ምላሾች ይቀበሉ ያበረታቷቸው፤ ትክክለኛ ምላሾችንም እየገለጹላቸው ያብራሩላቸው፡፡
- ተማሪዎች በጥንድ/በቡድን (4/6ተማሪዎች ባልበለጠ) እንዲቀመጡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች የተሰጣቸውን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ ይደግፏቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቅጥያዎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እና ምሳሌዎችን በመስጠት ያበረታቷቸው፡፡

- ተማሪዎች ከባለቅጥያ ቃላት ውስጥ ቃላትን እና ቅጥያዎችን እንዲነጣጥሉ ያበረታቷቸው፡፡

- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

- ቀድመው የቅጥያ ማሳያ ቻርቶችን (ሻሽ ቦርዶችን) እና የባለቅጥያ ቃላት ማሳያ ካርዶችን በማዘጋጀት እና ክፍል ይዞ በመምጣት ልጆች ተራ በተራ እየተነሱ የመነሻ እና የመድረሻ ቅጥያዎች መሆናቸውን እየለዩ በየምድባቸው እንዲያስቀምጡ ያበረታቷቸው፡፡

- ተማሪዎች ከተዘረዘሩት ባለቅጥያ ቃላቱ ውስጥ የመነሻ ቅጥያን የያዙ ወይም የመድረሻ ቅጥያን የያዙ መሆናቸውን በመለየት በየምድባቸው እንዲስቀምጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው


- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር:**

- ተማሪዎች ስለቅጥያዎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ቅጥያዎችን በመጠቀም ቃላትን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## ረ. የቀለም እና የቁጥር ቅደም ተከተል በመከተል የቤተሰብ አቆጣጠርን ተራ በተራ በስማቸው ቅደም ተከተል መልሶች፡፡

**መነሻ**



## ጽህፈት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለስም፣ ገላጭ እና ግስ ቃላት ምንነት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው።

- ተማሪዎች የተሰጣቸውን ቃላት በማገጣጠም ስም፤ ገላጭ እና ግስን የያዘ ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ምሳሌዎችን በመስጠት ያበረታቷቸው።

- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያንብቡላቸው፤ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው።

---

✓ ተማሪዎች ስለ ንግግር የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፣ በመቀጠል በቡድን እንዲደራጁ በማድረግ ስለ ትምህርትቤታቸው የተማሪዎች ሕግና ደንብ የትምህርትቤታቸውን ርዕሰ መምህር ወይንም የሚመለከተው አካል በማናገር እና መረጃ በመሰብሰብ ክፍል በማቅረብ እንዲወያዩ አስቀድመው የቤት ሥራ ይስጧቸው።

## ንግግር

**መምህር፡**

- ❖ ተማሪዎች ስለ ንግግር የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፣

- ❖ በመቀጠል በቡድን ሆነው ስለ ትምህርትቤታቸው የተማሪዎች ሕግና ደንብ የሰበሰቡትን መረጃ ለክፍል ጓደኞቻቸው ተራ በተራ ተከፋፍለው እንዲያቀርቡ በማድረግ የንግግር ክሂላቸው እንዲዳብር ያድርጉ። ያበረተቷቸው።

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ባሉ ምዕራፎች ለአቀላጥፎ ንባብ በተዘጋጁ ምንባቦች የንባብ ትክለኛነትን እና ፍጥነትን እንዲለማመዱ ተደርጓል፡፡ **በዚህ ምዕራፍ ደግሞ** ተማሪዎች ቃላትን በሚገባ ወይም **በትክክል እና በፍጥነት** ከማንበብ በዘለለ ተገቢውን **አገላለጽ** በመጠበቅ እንዲያነቡ በማድረግ ንባብን እንዲያዳብሩ ያድርጓቸው፡፡

- በተማሪ መጽሀፍ ላይ **"ሞኟ አህያ"** በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሁፍ ተማሪዎች በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) በተናጠል በመደጋገም እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

- እርስዎ **ትክለኛነት፣ ፍጥነት እና አገላለጽን** ያሟላ አነባበብ በማንበብ በቅድሚያ ያሳዩቸው፡

- ተማሪዎች ባሉበት ሆነው ድምጻቸውን እያሰሙ ተራ በተራ ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ እና እርስ በእርስ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡

- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ በሚሰጧቸው ደቂቃ ውስጥ ከጓደኞቻቸው ፊት በመሆን **"ትክክለኛነትን እና ፍጥነትን በመከተል በተለይ አገላለጽን በሚገባ እየተለማመዱ ማንበባቸውን"** እየተከታተሉ ጽሁፉን ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

## የምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያ

**መምህር**

ተማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የምዕራፉን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ መረዳታቸውን በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተቀመጡትን የምዕራፉን ማጠቃለያ ጥያቄዎች እንዲሰሩ በማድረግ ያረጋግጡ፤ እንዲሁም ከምዕራፉ ይዘት ጋር የሚገናኙ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመስጠት የምዕራፉን ትምህርት ያጠቃሉ፡፡

- ✓ በዚህ ምዕራፍ ስር አዳምጦ እና አንብቦ የመረዳትን፣ የመናገር እና የጽህፈት ክሂሎችን አዳብረዋል፡፡
- ✓ ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍቺ ሰጥተዋል፡፡
- ✓ ቅጥያዎችን ከሌሎች ቃላት መለየት ችለዋል፡፡
- ✓ ቅጥያዎችን ከቃላት ጋር በማጣመር ባለቅጥያ ቃለትን መጻፍ ችለዋል፡፡
- ✓ ተማሪዎች የንግግር ምንነትን አውቀዋል፡፡
- ✓ በተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ መረጃዎችን በመሰብሰብ የንግግር መመሪያዎችን ተከትለው ንግግር አድርገዋል፡፡
- ✓ ስም፣ ገላጭ  እና ግስን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን መመስረት ችለዋል፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ (፱)

## መናገኛ ብዙኃን

**የተሰጠ ክፍለ ጊዜ 9**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- በመቅረጸ ድምጽ ያዳመጡትን ዋና ሃሳብ ይናገራሉ፡፡
- አንብበው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡
- ነጠላ አረፍተነገሮችን በመጠቀም አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- ጥገኛ መስተጻምርን ተጠቅመው አረፍተነገር ያዋቅራሉ፡፡

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ማዳመጥእና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መጻፍ



### ማዳመጥ

### የሚኒ ሚዲያዋ ፍሬ

**መምህር፡**

- "**የሚኒ-ሚዲያዋ ፍሬ**" የሚለውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡
- "**የሚኒ-ሚዲያዋ ፍሬ**" የተሰኘውን ምንባብ የዝግታ ንባብ ስልትን በመጠቀም በእርጋታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ቀድመው ምንባቡን ኮፒ አድርገው በመስጠት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ በሚገባ እያዳመጡ መሆናቸውን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያረጋግጡ፡፡
- ተማሪዎች የተዘጋጀውን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## የሚኒ-ሚዲያዋ ፍሬ

ኤደን እባላለሁ። ዛሬ በቴሌቪዥን መስኮት ከምትመለከቷቸውና አንቱታን ከተቸሯቸው ሴት አንጋፋ ጋዜጠኞች ውስጥ አንዷ ነኝ። በየአመቱ በሚዘጋጀው የጋዜጠኞች ቀን ግንባር ቀደም ጋዜጠኛ በመባል በርካታ ሽልማቶች ተበርክተውልኛል።

ለዛሬው ሽልማቴና ለሥራዬ ስኬታማነት ደግሞ መሰረት የሆነኝ የተማሪነት ዘመኔ ነው። ተማሪ ሳለሁ በሚኒ-ሚዲያ ክበብ ከአባልነት እስከ ሰብሳቢነት የደረሰ ተሳትፎ ነበረኝ። የክበብ ተሳትፎየን "ሀ" ብዬ የጀመርኩት የአራተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ነበር።

የትምህርት ቤታችን የአማርኛ ቋንቋ መምህር በየክፍሉ እየዞሩ"የሚኒ-ሚዲያ ክበብ አባል መሆን የምትፈልጉ መመዝገብ ትችላላችሁ።" የሚል መልዕክት እንዳስተላለፉ ነበር እጄን አውጥቼ የተመዘገብኩት። ከዛን እለት ጀምሬ የሚኒ-ሚዲያ ክበብ አባል ስለሆንኩ በንቃት መሳተፍ ጀመርኩ። ክበባት የተማሪዎች እምቅ ተሰጥኦ ማሳደጊያዎች ናቸው። ለእኔም የሚኒ-ሚዲያ ክበብ የጋዜጠኝነት ተሰጥዎዬን ፍንትው አድርጎ አሳይቶኛል።

> ሀ. የሚኒ-ሚዲያ ተሳትፎዋን የጀመረችው የስንተኛ ክፍል ተማሪ እያለች ነው?
>
> ለ. የባለታሪካ መጨረሻ ምን ለ ሆን ይችላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ዘወትር ሰኞ በሚኒ-ሚዲያ ክበብ ዜና የሚቀርብበት ቀን ነው። ዜና የማቅረቡ ኃላፊነት ደግሞ ለእኔ ስለተሰጠኝ እሁድ ምሽት የሁለት ሰዓት ዜና በሬድዮ ሲቀርብ ሳሎን ቁጭ ብዬ ስከታተል አመሽና ዜናው እንዳበቃ ድምፄን እንደጋዜጠኛ በማስመሰል እለማመዳለሁ።
ልምምድና ዝግጅቴን አጠናቅቄ ጠዋት መድረክ ላይ ስወጣ ተማሪዎችና መምህራን በጭብጨባ ይቀበሉኛል። ዜናውን ማንበብ ስጀምር ሁሉም ፀጥ ብሎ ያዳምጠኛል። አንብቤ እንደጨረስኩ በድጋሚ በጭብጨባ አድናቆታቸውን ይገልጹልኛል። የሚኒ-ሚዲያ ክበብ ተግባሮችንም ከዕቅድ እስከፍፃሜ ከሌሎች አባላት ጋር በመነጋገርና በመግባባት በፕሮግራም ስንሰራ ስለነበር የክበቡን አቅምና ተወዳጅነት ማጎልበት ቻልን። ትምህርትቤታችን በአመቱ መጨረሻ ላይ የክበባትን የሥራ እንቅስቃሴ በማስመልከት ባደረገው የመዝጊያ መርሀ-ግብር ላይ የሚኒ-ሚዲያ ክበብ የአመቱ ምርጥ ክበብ በመባል ዋንጫ ሲሸለም ክበቡን ወክዬ ዋንጫውን ተቀብያለሁ።

ከዚያ በኋላ ትምህርቴን እስካጠናቅቅ ድረስ በሚኒ-ሚዲያ ክበብ በዜና አንባቢነትና አዘጋጅነት እየተሳተፍኩ፣ ከክበቡ አባላትም ጋር በቡድን የመሥራት ልምድ እያገኘሁ መጣሁ፡፡ ዛሬ አንድን ጉዳይ በጥሩ ሁኔታ ለማዘጋጀት ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር እርስበርስ የምናበበውና የምተባበረውም ከሚኒ-ሚዲያ ክበብ ባገኘሁት ተሞክሮ ተነስቼ ነው፡፡

በክበቡ በማቀርባቸው እንደ ስፖርትና ወቅታዊ ጉዳዮች ያሉ ተግባራት ከመቅረባቸው በፊት በጉዳዩ ዙሪያ መወያየት፣ መናበብ፣ ማረምና ማስተካከል እንደሚገባ ተምሬበታለሁ፡፡ ከትምህርትቤታችን የሚኒ-ሚዲያ ክበብ ያገኘሁት ልምድና ተሞክሮ በሥራዬ ስኬታማ እንድሆን ትልቁን ድርሻ ይዟል፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲመርጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች የቃላት ዕውቀታቸውን እንዲያዳብሩ የተለየዩ አገላለጾችን እንዲለማመዱ የተለየዩ ጥያቄዎችነ እና ምሳሌዎችን በመስጠት ያበረታቷቸው፡፡

**ምሳሌ፡-** ሀ. ነጭ ደመናን ስናይ ፡- ጥጥ የመሰለ_________እንላለን፡፡ (ደመና)

ለ. አንድ ጥሩ እጅ ጽሁፍ ስናይ፡- ቆሎ የመሰለ_______እንላለን፡፡ (እጅ ጽሁፍ)

ሐ. ድንቡሽቡሽ ያለ ጉንጭ ስናይ፡- ብርቱካን የመሰለ _________እንላለን፡፡ (ጉንጭ)

**መምህር፡**

- ለተሰጡት ምሳሌዎች መርጃ መሳሪያዎችን በማምጣት ከአገላለጹ ጋር ያላቸውን ትስስር ያስረዱዋቸው፡፡

**ምሳሌ፡-** በጠራ ሰማይ ላይ የምናየው ደመና ከለሩ ምን እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡ መልሳቸውንም ይቀበሏቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡

- ደመና ከለሩ ነጭ ነው፡፡ በተመሳሳይ ጥጥ ይዞ በመምጣት ለተማሪዎች ያሳዩቸው፤ ከለሩንም ይጠይቋቸው፡፡

- ጥጥ ከለሩ ነጭ ነው፡፡

ስለዚህ ጥጥ የመሰለ ደመና ስንል ደመናውን ከጥጡ ከለር እና ቅርጽ ጋር በማያያዝ/በማዛመድ መሆኑን ያስረዷቸው፡፡

**በተመሳሳይ፡-** ቆሎ የመሰለ እጅ ጽሁፍ ስንል የቆሎን መጠን ከጥሩ የእጅ ጽሁፍ ፊደል አጣል እና የፊደል መጠን ጋር በማያያዝ መሆኑን ያስረዷቸው፡፡

**እንዲሁም፡-** ሌሎችን አገላለጾችንም በዚህ መንገድ በሚገባ ያስረዷቸው፡፡

- ተመሳሳይ ምሳሌዎችን በመስጠት በክፍል ደረጃቸው ልክ ብቻ ያብራሩላቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በጥንድ/በቡድን(4/6 ተማሪዎች ባልበለጠ) እንዲቀመጡ ያድርጉ፤
- በተመሳሳይ ለስላሳ ጨርቅ (ከተቻለ ከሃር የተሰራ ልብስ /የሃር ጨርቅ ቁራጭ) የረጅም ጸጉር፣ በብርጭቆ ውስጥ ያለ የጠለለ ጠላ፣ የበረዶ፣ የነጭ ጥርስ፣ በብርጭቆ ያለ ውሃ፣ የስንደዶ እና ኢትዮጵያዊ የዓይን ምስሎችን በቅድሚያ በኤ 1 ወረቀት ላይ ቀድሞ በመለጠፍ እና መርጃ መሳሪያ በማዘጋጀት እንዲሁም ወደ ክፍል በማምጣ እና ለሁሉም ተማሪዎች በሚታይ ቦታ ላይ በማንጠልጠል ተማሪዎች ከለራቸውን/ ቅርጻቸውን እንዲመለከቱበት ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- የተዘጋጀውንም ጥያቄ በሚሰሩበት ጊዜ ድጋፍ ያድርጉላቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ሐ. ለአገላለጾች የተሰጡ መልሶች፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ቡና | 3. አፍንጫ | 5. ዓይን | 7. ውሃ |
| 2. ጥርስ | 4. ጠላ | 6. ጸጉር | |

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለወደረኛ እና ጥገኛ መስተጻምር የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እና ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲሁም በምሳሌዎች በማብራራት እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በጥንድ/በቡድን (4/6ተማሪዎች ባልበለጠ) እንዲቀመጡ ያድርጉ፡፡
- ከተሰጡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ወደረኛ እና ጥገኛ መስተጻምሮችን እንዲያወጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለወደረኛ እና ጥገኛ መስተጻምር የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እና ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲሁም በምሳሌዎች በማብራራት እና ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት ያሳዩቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ወደረኛ መስተጻምሮችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለአያያዥ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እና ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲሁም በምሳሌዎች በማብራራት፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ከዓረፍተነገሮች ውስጥ አያያዥ ቃላትን በመለየት እንዲያወጡ ያድርጉ፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ንባብ

## የሚዲያ ፈርጦች

**መምህር፡**

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ "**የሚዲያ ፍርጦች**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት ቀደምት ዕውቀታቸውን በመጠቀም የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡

- ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

- "**የሚዲያ ፈርጦች**" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ለእነዚህ ተማሪዎች ለብቻቸው እርስዎ በዝግታ የንባብ ስልት ያንብቡላቸው፡፡

- ተማሪዎች ለድህረ ንባብ የቀረቡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## መናገር

**መምህር፡**

- በተማሪዎች የክፍል ደረጃ መሰረት ከመገናኛ ብዙሃን ከ3-5ደቂቃ ያልበለጠ መረጃን በድምጽ በመቅዳት ለተማሪሪዎች እንዲያዳምጡ ያዘጋጁ፤ ርዕሰ ጉዳዩ፡-

  ምሳሌ፡- ስለአካባቢ ጥበቃ

  ስለ ስፖርት

  ስለ ትምህርት

  ስለ አብሮነት. . . ሃሳቦችን የያዙ እና ከተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ ያልበለጡ መሆናቸውን በቅድሚያ ያረጋግጡ፡፡
- (የሚቻል ከሆነ ከምስል ጋር የተደገፈ ቢሆን ይበልጥ መስማት የተሳናቸውን ተማሪዎች ከመደገፍ ባለፈ የሌሎችንም ተማሪዎች የመረዳት አቅማቸውን ያጎለብታልና አማረጩ ካለዎት ከምስል ጋር የተደገፈ የሚደመጥ መረጃን ያዘጋጁ)
- ተማሪዎች የተዘጋጀውን መረጃ ካዳመጡ በኋላ ዋና ሃሳቡን በተመለከተ ለክፍል ተማሪዎች ተራ በተራ እንዲያብራሩ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ስለሚቀርበው ርዕሰ ጉዳይ የተመለከተ ጽሁፍን በቅድሚያ በማዘጋጀት እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ የጽሁፉን ዋና ሃሳብ በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ተመሳሳይ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- በምንባቡ መሰረት ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ሀ. የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መልሶች፡፡

1. ጥንካሬ
2. አበርክቶ
3. አጋዥ /ደጋፊ
4. ማጠናቀቂያ
5. መርሳት
6. ማሳደግ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ተቃራኒ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ጽህፈት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓረፍተነገር የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው ያበረታቷቸው፤
- ተማሪዎች በተሰጧቸው ቃላት ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለነጠላ ዓረፍተ ነገር የተማሩትን እንዲያስታሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡ የተለዩዩ ጥያቄዎችንም ይጠይቋቸው፡፡

  **ምሳሌ፡-** ምን እያደረጋችሁ ነው? እኛ እየተማርን ነው፡፡ ፤ እኛ እየጻፍን ነው፡፡. . .

  ወደ ትምህርትቤት በምን መጣችሁ? እኔ በእግሬ መጣሁ፡፡ ፤ እኔ በመኪና መጣሁ፡፡

  እድሜህ/ዕድሜሽ ስንት ነው? ዕድሜዬ 10 ዓመት ነው፡፡. . .

- ተማሪዎች ዓረፍተነገሮቹን በሚመሰርቱበት ጊዜ አንድ ግስ ብቻ እየተጠቀሙ መሆናቸውን ይከታተሉ ድጋፍም ያድርጉላቸው፡፡
- በተሰጧቸው ቃላት ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለውስብስብ ዓረፍተ ነገር የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው።

- ተማሪዎች ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው። የተለዩዩ ጥያቄዎችንም ይጠይቋቸው።

  **ምሳሌ፡-** ስምህን እና ዕድሜህን ንገረኝ/ሪኝ? ስሜ "ቃልኪዳን" ይባላል፤ዕድሜዬ 10 ዓመት ነው።

  ወደቤት ስትመለሱ ምን ታደርጋላችሁ? ዩኒፎርሜን ቀይሬ አጠናለሁ። . . .

- ተማሪዎች ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮቹን በሚመሰርቱበት ጊዜ ሁለትና ከዛ በላይ ግሶችን እየተጠቀሙ መሆናቸውን ይከታተሉ ድጋፍም ያድርጉላቸው።
- የተሰጧቸውን ቃላት በማገጣጠም ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ድጋፍ ያድርጉላቸው።
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው።

## ሐ. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት በመጠቀም የተመሰረቱ ሶስት ውስብስብ ዓረፍተነገሮች መልሶች።

1. ወንድሙን ይዞ ተመለሰ።
2. ሰኞ ማክሰኞ ጨዋታ ተጫውተው ስንጨርስ አጠናን።
3. ለወላጆቻችን በመታዘዝ ምርቃት ተቀበልን።

**መምህር፡**

- ✓ ተማሪዎች ስለተራ ዓረፍተ ነገር እና ስለአንቀጽ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እና ምሳሌዎችን በመስጠት ያበረታቷቸው፡፡

- ➢ ተማሪዎች በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተሰጠውን "የልጆች ጨዋታ- መጬ ተኬ" የሚለውን ምሳሌ በሚገባ እንዲረዱ ተመሳሳይ ምሳሌዎችን በመስጠት ያስረዷቸው፡፡
- ➢ ተማሪዎች ከ5-7 ነጠላ ዓረፍተነገሮች በመጠቀም አንቀጽ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

ምሳሌ፡- - የልጆች ጨዋታ
- ስለ ንባብ ጥቅም
- ስለት/ቤታቸው ገጽታ. . .

- ➢ በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

- ➢ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ባሉ ምዕራፎች ለአቀላጥፎ ንባብ በተዘጋጁ ምንባቦች የንባብ ትክለኛነትን እና ፍጥነትን እንዲለማመዱ ተደርጓል፡፡ **በዚህ ምዕራፍ ደግሞ** ተማሪዎች ቃላትን በሚገባ ወይም **በትክክል** እና **በፍጥነት** ከማንበብ በዘለለ ተገቢውን **አገላለጽ** በመጠበቅ እንዲያነቡ በማድረግ ንባብን እንዲያዳብሩ ያድርጓቸው፡፡
- ➢ በተማሪ መጽሀፍ ላይ " **ስግብግቡ አይጥ"** በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሁፍ ተማሪዎች በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) በተናጠል በመደጋገም እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

## አቀላትፎ ማንበብ

**መምህር፡**

- እርስዎ **ትክክለኛነት፣ ፍጥነት እና አገላለጽን** ያሟላ አነባበብ በማንበብ በቅድሚያ ያሳዩቸው፡፡

- ተማሪዎች ባሉበት ሆነው ድምጻቸውን እያሰሙ ተራ በተራ ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ እና እርስ በእርስ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡

- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ በሚሰጧቸው ደቂቃ ውስጥ ከጓደኞቻቸው ፊት በመሆን **"ትክክለኛነትን እና ፍጥነትን በመከተል በተለይ አገላለጽን በሚገባ እየተለማመዱ ማንበባቸውን"** እየተከታተሉ ጽሁፉን ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ተገቢውን **የንባብ አገላለጽን** ተከትለው ማንበባቸውን ይከታተሉ፤ ማስታወሻዎችንም በመያዝ በተገቢው የፍጥነት ደረጃ ያላነበቡ ተማሪዎችን የሚደግፉበት ስልት በመቀየስ የንባብ ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ ይደግፏቸው፡፡

- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ንባቡን እንዲያዳምጡ በማድረግ የምንባቡ ሃሳብ ስለምን እንደሆነ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተዘረዘሩትን የሰውነት ክፍሎች በግእዝ ስያሜያቸው ምን እንሚባሉ እንዲያጠኑ ያበረታቷቸው፤
- ተማሪዎች እርስ በእርስ እየተራረሙ ልምምድ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ እርስዎ እያነበቡላቸው ስያሜያቸውን እንዲያውቁ ያበረታቷቸው፡
- ተማሪዎች የተለማመዱትን የሰውነት ክፍሎች የግዕዝ ስያሜ በቃላቸው በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

## የምዕራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያ

**መምህር**

ተማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የምዕራፉን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ መረዳታቸውን በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተቀመጡትን የምዕራፉን ማጠቃለያ ጥያቄዎች እንዲሰሩ በማድረግ ያረጋግጡ፤ እንዲሁም ከምዕራፉ ይዘት ጋር የሚገናኙ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመስጠት የምዕራፉን ትምህርት ያጠቃሉ።

- ✓ በዚህ ምዕራፍ ስር አዳምጦ እና አንብቦ የመረዳትን፣ የመናገር እና የጽህፈት ክሂሎችን አዳብረዋል።
- ✓ ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍቺ ሰጥተዋል።
- ✓ የነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ምንነትን ማስታወስ ችለዋል።
- ✓ ነጠላ ዓረፍተነገሮችን በመጠቀም አንቀጽ ጽፈዋል።
- ✓ ወደረኛ መስተጻምሮችን በመጠቀም አረፍተነገር አዋቅረዋል።

**ለማጠቃለያ ጥያቄ የአገላለጽ መልሶች።**

ሀ. ድሪ የመሰለ______አረቄ______ እንላለን።

ለ. ሳንቃ የመሰለ______ደረት______እንላለን።

ሐ. ብርሌ የመሰለ______አንገት______እንላለን።

መ. አለንጋ የመሰለ ጣት እንላለን።

-

# ምዕራፍ  አስር (፲)

## ንግድ

**የተሰጠ ክፍለ ጊዜ 9**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጠናቀቅ በኂላ ተማሪዎች፡-**

- አዳምጠው በቡድን ውይይት ያደርጋሉ፤
- ካነበቡት ጽሁፍ ውስጥ ከእያንዳንዱ አንቀጽ ዋናውን ሃሳብ ይለያሉ፤
- በተሰጣቸው ርእስ አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- ከአንድ በላይ ፍቺ ያላቸውን ቃላት ይፈልጋሉ፤
- ቅጥያዎችን ተጠቅመው አረፍተነገር ይመሰርታሉ፤

**የምዕራፉ ይዘቶች፡-**

- ማዳመጥ እና መናገር
- ማንበብ
- ቃላት
- መጻፍ



### ማዳመጥ

### ንግድ

**መምህር፡**

- "ንግድ" የሚለውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሚሰጧቸው ምላሾች ያበረታቷቸው፡፡
- "ንግድ" የተሰኘውን ምንባብ የዝግታ ንባብ ስልትን በመጠቀም በእርጋታ እና በተመጠነ የድምጽ ደረጃ ያንብቡላቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ቀድመው ምንባቡን ኮፒ አድርገው በመስጠት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ በሚገባ እያዳመጡ መሆናቸውን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያረጋግጡ፤
    - ተማሪዎች የተዘጋጀውን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፤

## ንግድ

የንግድ ሥራ ማለት በተከታታይ ወይም ባጭር ጊዜ ለትርፍ የሚከናወን ማንኛውም የኢንዱስትሪ፣ የሆቴል፣ የሸቀጣሸቀጥ. . . ሥራዎችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ንግድ ለራስ ሥራ መፍጠርና ትርፍ ማግኘት ብቻ ሳይሆን ለህብረተሰቡም ችግር መልስ የሚሰጥ መሆን አለበት፡ ፡ የንግድ ሃሳብ በምናስብበት ጊዜ በዘፈቀደ ይህኛው ይሻላል፣ ይህኛው አይሆንም የምንለው ሳይሆን አስፈላጊ መመዘኛዎችን በማስቀመጥ መምረጥ አለብን፡፡ ምክንያቱም በንግድ ሥራ ውስጥ በርካታ ለስኬት አጋዥ የሆኑ እንደገንዘብና ጥሩ የንግድ ዕውቀት እንዲሁም ሌሎች ውጫዊ ነገሮች ተስተካክለው ቢኖሩም ለስኬት ወሳኝ የሆኑ ጥሩ የንግድ ሰው ባሕርያት ካልታከሉበት ውጤቱ ወይም እድገቱ አጥጋቢ አይሆንም፤ ኪሳራ ሊሆንም ይችላል፡፡

ስለዚህ በንግድ ሥራ ውስጥ ተወዳዳሪና ስኬታማ ለመሆን ግላዊ የሥራ ፈጠራ ክህሎታችንን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ የሥራ ፈጠራን ለውጤት ለማብቃት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ የሚባሉት ባሕርያት በአብዛኛው ለስኬታማነት ከመነሳትና ለውጤት ከመጣር የመነጩ ናቸው፡፡

ለውጤት የተነሳ ግለሰብ ባሕርያት የሚባሉትን ብዙዎች ሲዘረዝሯቸው፡- የቴክኒክ ብቃት፣ ተነሳሽነት፣ የንግድ ዕውቀት፣ የመምራት ብቃት፣ በራስ መተማመን፣ ጥንካሬ፣ ጥሩ አመለካከት፣ ደንበኛን ማክበር፣ ቀጠሮ ማክበር፣ ጠቃሚ ነገሮችን መፈለግ፣ አዳዲስ ሃሳብ ማመንጨትና የመፍጠር ችሎታ፣ እዉነተኛነት ፣ ግልፅ የሆነና ሌሎችን በተገቢው ሁኔታ መዳኘት የሚችል ወዘተ ናቸው፡፡

ሀ. የንግድ ስራ ማለት ምን ማት ነው?

ለ. የስራ ፈጠራ ባሕርያት የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

ዋና ዋናዎቹ ውጤታማ የሥራ ፈጠራ ግላዊ ባሕርያት ተብለው የተቀመጡት፤ ጥሩ አጋጣሚን መጠቀምና ተነሳሽነት፣ ተስፋ ያለመቁረጥ(ፅናት)፣ በጥራትና በቅልጥፍና መሥራት፣ አስቀድሞ መዘጋጀት፣ ውልን ማክበር፣ መረጃን መጠቀም፣ ግብ መንደፍ፣ በዘዴ ማቀድና መገምገም፣ ሰዎችን ማሳመንና ግንኙነት መፍጠር እንዲሁም በራስ መተማመን ናቸው፡፡

በንግድ ሥራዎች ውስጥ እነዚህን ባሕርያት የምንጠቀም ከሆነ በሥራችን መሻሻልን እናሳያልን፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደተገለጸው ገንዘብ፣ ዕውቀት ወይም ሌሎች ንግድን ለመጀመር አስፈላጊ

ቢሆኑም ገንዘብ ስላለን ወይም የሥራ ዕውቀት ብቻ ለውጤት አያበቃንም፡፡ ስለዚህ በንግድ ሥራችን ውስጥ በዘላቂነት ለመቆየትና እድገት ለማሳየት የተዘረዘሩትን ባሕርያት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ባሕርያትን መማር፣ ማሻሻል፣ መልመድ፣ እንዲሁም በሥራችን ላይ መተግበር ይኖርብናል፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ አንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲመርጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለአንቀጽ ምንነት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለየዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- በተማሪ መጽሐፍ ላይ የሚገኘውን የአንቀጽ ምሳሌ መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የአንቀጹን ዋና ሃሳብ እንዲለዩ ያበረታቷቸው፡፡
- በተመሳሳይ ለተማሪዎች የክፍል ደረጃ ሚመጥኑ የተለየዩ ነጠላ አንቀጾችን በማምጣት ዋና መልዕክቱን እንዲናገሩ ወይም ለይተው እንዲጽፉ ያበራቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎችን በጥንድ/በቡድን (4/6 ተማሪዎች ባልበለጠ) እንዲቀመጡ ያድርጉ፡፡

- በተማሪ መጽሀፍ ላይ ተሰጡትን አንቀጾች ዋና መልዕክት/ሃሳብ እንዲለዩ ያበረታቷቸው፡፡ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**የአንቀጽ ዋና መልዕክት(ሃሳብ) መልሶች፡፡**

1. የገበጣ ጨዋታ ምንነት
2. የመደበኛ ትምህርት ምንነት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለአንቀጽምንነት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለየዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ የሚገነውን የአንቀጽ ምሳሌ ከስዕሉ ጋር በማነጻጸር/በማዛመድ በሚገባ እንዲያነቡና እንዲረዱ ያበረታቷቸው፤ ድጋፍም ያድርጉላቸው፡፡

- በተመሳሳይ ለተማሪዎች የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ የተለያዩ ነጠላ ሃሳብን የሚያብራሩ አንቀጾችን በምሳሌነት ያሳዩቸው፤ ያብራሩላቸው፡፡

- ተማሪዎችን በጥንድ/በቡድን (4/6 ተማሪዎች ባልበለጠ) እንዲቀመጡ ያድርጉ፡፡

- በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተሰጠውን የአንቀጽ ምሳሌ መሰራት በማድረግ ምስሎቹን በተመለከተ በእያንዳንዳቸው አንድ፤ አንድ አንቀጽ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃል እዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ንባብ

### መልካም ሰው

**መምህር፡**

- በተማሪ መጽሐፍ ላይ "**መልካም ሰው**" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት ቀደምት ዕውቀታቸውን በመጠቀም የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡

- ተማሪዎች ለተወሰኑ ደቂቃዎች ባሉበት ሆነው በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) የዝግታ ንባብ ስልትን በመተቀም እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

- "**መልካም ሰው**" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ለእነዚህ ተማሪዎች ለብቻቸው እርስዎ በዝግታ የንባብ ስልት ያንብቡላቸው፡፡

- ተማሪዎች ለድህረ ንባብ የቀረቡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡

## መናገር

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ባሉበት ሆነው ድምጻቸውን ሳያሰሙ (በአርምሞ) የዝግታ የንባብ ስልትን በመጠቀም ምንባቡን በድጋሚ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች የምንባቡን መልዕክት ወይንም ዋና ሐሳብ በጽሁፍ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነስውራን ተማሪዎች ካሉ ምንባቡን እርስዎ ለብቻቸው የዝግታ የንባብ ስልትን በመጠቀም ያንብቡላቸው፡፡
- በዋናው መልዕከት/ሐሳብ ላይ የቡድን ውይይት በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ የምንባቡን ዋና ሐሳብ ወይን መልዕክት በቃላቸው እንዲያስረዱ ያበረታቷቸው፡፡

## ቃላት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ተመሳሳይ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- በምንባቡ መሰረት ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

### ሀ. የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መልሶች፡፡

1. በብዛት መምጣት
2. መያዝ
3. መልካም (ጥሩ)
4. በዛ
5. ማጠራቀም

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ተቃራኒ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ እርማትም ይስጧቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

1. ጥፋት
2. አስገባ
3. ዕለት
4. ከሰረ
5. መምጣት

## ጽህፈት

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ቃላትን በማጥበቅ እና በማላላት ስናነባቸው የሚሰጡትን የተለያየ ትርጉም እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው ያበረታቷቸው፤

- ተማሪዎች የተሰጧቸው ቃላት በመጥበቅ እና በመላላት ሲነበቡ የሚኖራቸውን ትርጉም የሚያሳይ ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለ ቅጥያዎች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ይጠይቋቸው፤ ያበረታቷቸው፤
- ተማሪዎች ከተሰጧቸው ባለቅጥያ ቃላት ውስጥ ቃላትን እና ቅጥያዎችን በመነጣጠል እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ እርማትም ይስጧቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቃላት ዓይነቶች የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ቃላቱን በየምድባቸው እንዲያስቀምጡ ያበረታቷቸው፡፡

በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለዓረፍተ ነገር እና ባለቅጥያ ቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በተሰጧቸው ባለቅጥያ ቃላት ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለቃላት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች ቃላት በመጥበቅ እና በመላት ሲነበቡ ብቻ ሳይሆን በሚገቡበት ዓረፍተ ነገር ውስጥ ከሌሎች ቃላት ጋር ሲሆኑ የትርጉም ለውጥ እንደሚኖራቸው ያብራሩላቸው፡፡

  ምሳሌ፡- ሳለ የሚለውን ቃል በመጠቀም፡-

  ሰዓሊው ስዕል ሳለ፡፡ (ትርጉሙ ፡- የስእል ቁሳቁሶችን በመጠቀም ምስል ቀረጸ አሰፈረ ማለት ነው)

  ልጁ ሳለ፡፡ (ትርጉሙ፡- ጉንፋን የመያዝ ድምጽ አሰማ)
- በተመሳሳይ መሰል ምሳሌዎችን ያስሯቸው፡፡
- ተማሪዎች በጥንድ(በቡድን4/6 ተማሪዎች ባልበለጠ) እንዱቀመጡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች በተሰጧቸው ቃላት በዓረፍተነገር ሲገቡ የሚኖራቸውን የተለያየ ትርጉም የሚያሳይ ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡
  - በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ሠ.ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ የሚሰጡትን የተለያየ ትርጉም መልሶች

1. ጠላ (ባህላዊ መጠጥ) እና (መጥፎ ስሜት አደረበት)
2. አሰሰ (መጥረግ) እና (መፈለግ)
3. ሳሳ (ተንሰፈሰፈ) እና (ውፍረቱ ቀነሰ)
4. ስጋ (ዘመድ) እና (የእንስሳት ተዋጽኦ/ ምግብ)
5. ቀጠፈ (ዋሸ) እና (ቆረጠ)

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ስለነጠላ ዓረፍተ ነገር የተማሩትን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች በጥንድ በቡድን (4/6 ተማሪዎች ባልበለጠ) እንዲቀመጡ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች **"አርባ ምንጭ"** በሚል ርዕስ በቀረበው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙትን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን ለይተው እንዲያወጡ ያበረታቷቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ በቃላቸው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ረ. "አርባ ምንጭ" በሚል ርዕስ ውስጥ ለሚገኙ ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች መልስ፡፡

1. በአርባ ምንጭ በስፋት ሙዝ ይመረታል፡፡
2. በተጨማሪምበዚሁ ዞን የአፕል ምርት በስፋት ይመረታል፡፡
3. በመኪና በመጫን በአገሪቱ ላሉ የተለያዩ አካባቢዎች ያደርሳሉ፡፡

4 አርሶ አደሩም ፍራ ፍሬዎችን በማምረት በከፍተኛ ሁኔታ ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መምህር፡**

- ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ባሉ ምዕራፎች ለአቀላጥፎ ንባብ በተዘጋጁ ምንባቦች የንባብ ትክለኛነትን እና ፍጥነትን እንዲለማመዱ ተደርጓል፡፡ **በዚህ ምዕራፍ ደግሞ** ተማሪዎች ቃላትን በሚገባ ወይም **በትክክል እና በፍጥነት** ከማንበብ በዘለለ ተገቢውን **አገላለጽ** በመጠበቅ እንዲያነቡ በማድረግ ንባብን እንዲያዳብሩ ያድርጓቸው፡፡
- በተማሪ መጽሀፍ ላይ " **አህያ እና ውሻ"** በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሁፍ ተማሪዎች በአርምሞ (ድምጻቸውን ሳያሰሙ) በተናጠል በመደጋገም እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- እርስዎ **ትክክለኛነት፣ ፍጥነት እና አገላለጽን** ያሟላ አነባበብ በማንበብ በቅድሚያ ያሳዩቸው፡፡
- ተማሪዎች ባሉበት ሆነው ድምጻቸውን እያሰሙ ተራ በተራ ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ እና እርስ በእርስ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ በሚሰጧቸው ደቂቃ ውስጥ ከጓደኞቻቸው ፊት በመሆን **"ትክክለኛነትን እና ፍጥነትን በመከተል በተለይ አገላለጽን በሚገባ እየተለማመዱ ማንበባቸውን"** እየተከታተሉ ጽሁፉን ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡
- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ተገቢውን **የንባብ አገላለጽን** ተከትለው ማንበባቸውን ይከታተሉ፤ ማስታወሻዎችንም በመያዝ በተገቢው የፍጥነት ደረጃ ያላነበቡ ተማሪዎችን የሚደግፉበት ስልት በመቀየስ የንባብ ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ ይደግፏቸው፡፡
- በክፍል ውስጥ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች ካሉ ንባቡን እንዲያዳምጡ በማድረግ የምንባቡ ሃሳብ ስለምን እንደሆነ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

## የምዕራፍ አስር ማጠቃለያ

**መምህር**

ተማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የምዕራፉን የትምህርት ይዘቶች በሚገባ መረዳታቸውን በተማሪ መጽሀፍ ላይ የተቀመጡትን የምዕራፉን ማጠቃለያ ጥያቄዎች እንዲሰሩ በማድረግ ያረጋግጡ፤ እንዲሁም ከምዕራፉ ይዘት ጋር የሚገናኙ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመስጠት የምዕራፉን ትምህርት ያጠቃሉ።

በዚህ ምዕራፍ ስር አዳምጦ እና አንብቦ የመረዳትን፣ የመናገር እና የጽህፈት ክሂሎችን አዳብረዋል።

- ✓ ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍቺ ሰጥተዋል።
- ✓ ከአንቀጽ ውስጥ ዋና ሃሳብን መለየት ችለዋል።
- ✓ የቃላትን አንድ በላይ ፍቺ በመለየት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ተጠቅመው አሳይተዋል።
- ✓ ቅጥያዎችን ተጠቅመው ዓረፍተነገር መስርተዋል።
- ✓ በተሰጣቸው ርዕስ አንቀጽ መጻፍ ችለዋል።

**ለማጠቃለያ ጥያቄ የአገላለጽ መልሶች።**

ሀ. ቆረጠ ፡- ወሰነ እና አስተካከለ ፣ከረከመ አሳጠረ

ለ. ሰፋ፡- ጠገነ (መርፌ እና ክር አገናኘ) እና መጠኑ ጨመረ

ሐ. ገዛ ፡- ሸመተ/ገበየ እና አስተዳደረ/መራ

መ. ምሳ፡- ቆፍራ እና እኩለ ቀን ላይ የምንመገበው ምግብ መጠሪያ

ሠ. አረረ፡- ተናደደ እና በእሳት ተቃጠለ

የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

## የፊደል ቅደም ተከተል

ሀ. የመጀመሪያ ፊደል = ግዕዝ

ሁ. ሁለተኛ ፊደል = ካዕብ

ሂ. ሦስተኛ ፊደል = ሣልስ

ሃ. አራተኛ ፊደል = ራብዕ

ሄ. አምስተኛ ፊደል = ኃምስ

ህ. ስድስተኛ ፊደል = ሳድስ

ሆ. ሰባተኛ ፊደል = ሳብዕ

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 1 | ፪ 2 | ፫ 3 | ፬ 4 | ፭ 5 | ፮ 6 | ፯ 7 | ፰ 8 | ፱ 9 | ፲ | 10 |
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | 100 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፻ | 100 | ፳፻ | 2000 |
| ፪፻ | 200 | ፴፻ | 3000 |
| ፫፻ | 300 | ፵፻ | 4000 |
| ፬፻ | 400 | ፶፻ | 5000 |
| ፭፻ | 500 | ፷፻ | 6000 |
| ፮፻ | 600 | ፸፻ | 7000 |
| ፯፻ | 700 | ፹፻ | 8000 |
| ፰፻ | 800 | ፺፻ | 9000 |
| ፱፻ | 900 | ፼ | 10000 |
| ፲፻ | 1000 | ፻፼ | 1000000 |